# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 194 መጋቢት 14 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ ፡- ፀሐይ ንጉሴ

# ሕወሓት ከሽብርተኝነት መዝገብ መነሳቱ

## በትግራይ አካታች ጊዜያዊ አስተዳደር ለማቋቋም እንደሚረዳ ተገለጸ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ሕወሓትን ከሽብርተኝነት መዝገብ ማንሳት በትግራይ ሁሉንም አካታች ጊዜያዊ አስተዳደር ለማቋቋም እንደሚረዳ ተገለጸ። 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 2ኛ ዓመት 1ኛ ልዩ ጉባኤውን ትናንትና በማካሄድ ሕወሓትን ከአሸባሪነት ስያሜ ለማንሳት የቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ቁጥር 12/2015 በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል።

የፍትሕ ሚኒስትር ጌዲዮን ጢሞቴዎስ (ዶክተር)፤ ሕወሓትን ከሽብርተኝነት ፍረጃ ማንሳት በትግራይ አካታች የጊዜያዊ አስተዳደር ለማቋቋም ታስበው ለሚከናወኑ ሥራዎች ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል ሲሉ አስረድተዋል።

ሕወሓት ከፌዴራል መንግሥት ዕውቅና ውጪ ያካሄደው ምርጫና ያቋቋመው ክልላዊ መንግሥት ሕጋዊ እንዳልሆነ አውቆ በፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት መፈረሙን ገልጸዋል። በፕሪቶሪያውን የሰላም ስምምነት አንቀጽ 7/2 C መሠረት የፌዴራል መንግሥት

ሕወሓት ከሽብርተኝነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# «ጊዜው የትግራይን ልማትና መልሶ ግንባታ የምናበስርበት እንጂ ሥልጣን የምንሻማበት አይደለም»

- አብርሃም በላይ (ዶ/ር)
የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስትር

**ሄርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- "ጊዜው የትግራይን ልማትና መልሶ ግንባታ የምናበስርበት እንጂ ሥልጣን የምንሻማበት አይደለም" ሲሉ የመከላከያ ሚኒስትሩ አብርሃም በላይ (ዶ/ር) ገለጹ። ሁሉም ትግራዋይ በተለይ ወጣቱ ትውልድ አንድነቱን አጠናክሮ ለሕዝብና ለሀገር የሚተርፍ ሥራ ለመሥራት እንዲዘጋጅም ጥሪ አቅርበዋል።

ዶክተር አብርሃም የትግራይ ሕዝብ ያጋጠመው ችግርና መሰናክል ዘርፈ ብዙ መሆኑን ጠቁመው፤ ከዚህ ችግር ለመሻገር ከምንም ጊዜ በላይ የጠነከረ አንድነትና መተባበር

«ጊዜው የትግራይን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በክልሉ በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች 105 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ቀርቧል

## - በ7 ሚሊዮን ብር የእንስሳት መኖ ግዢ ተፈጽሟል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ክልል በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች ከ105 ሚሊዮን ብር በላይ የዓይነት ድጋፍ መቅረቡን የክልሉ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ። በሰባት ሚሊዮን ብር የእንስሳት መኖ ግዢ መፈጸሙም ተገልጿል።

የደቡብ ክልል አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ፋሲካ ዓለሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ

በክልሉ በድርቅ ለተጎዱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


















# ከሰላም ስምምነቱ

## በኋላ ሀገራት ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸው የልማት ትብብር ጨምሯል

ገጽ 4









ዜና

# ፋብሪካዎቹን ወደግል ማዛወር ምርታማነትን በማሳደግ ከውጭ የሚገባውን ስኳር ለማስቀረት ይረዳል

**አመስወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት የስኳር ፋብሪካዎችን ወደግሉ ዘርፍ ለማዞር የጀመረው ሥራ የፋብሪካዎቹን ምርታማነት ለማሳደግና ከውጭ የሚገባውን የስኳር ምርት ለማስቀረት ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል ሲሉ የዲላ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህሩና ተመራማሪ ዶክተር ዳዊት አዬሶ ገለጹ።

ዶክተር ዳዊት አዬሶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መንግሥት የኦሞ ኩራዝ ስኳር ፋብሪካዎችን፣ ፊንጫ፣ ወንጂ አርጆ ደዴሳ፣ ከሰም፣ ጣና በለስ እና ተንዳሆ ፋብሪካዎችን ወደግል ማዞሩ የፋብሪካዎቹን ምርታማነት ለማሳደግና ከውጭ ሀገራት ስኳር ለማስገባት የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ለማስቀረት ጉልህ ድርሻ አለው።

ፋብሪካዎቹ ከመንግሥት ይዞታነት ወደግል ዘርፍ ሲዞሩ በትርፋማነት ላይ ያተኮረ አሰራርን በይበልጥ ተግባራዊ ለማድረግ ያግዛል። የግል ባለሀብቱ ብዙ ምርት ባመረተ ቁጥር የበለጠ ካፒታል እንደሚያገኝ ስለሚያስብ የፋብሪካዎቹን ማሻሻያና ምርታማነት ላይ ያተኮረ ስራ ማከናወን ይችላል ብለዋል።

የስኳር ፋብሪካዎቹ ምርታማነት ጨመረ ማለት ደግሞ ኢትዮጵያ ከውጭ የምታስገባው ስኳር እንዲቀር ምክንያት ይሆናል። ይህም የውጭ ምንዛሪ ወጪን በማስቀረት ረገድ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

የግሉ ዘርፍ በተለምዶ እንደሚስተዋለው ያለውን ሀብት ከብክነት በጸዳ መልኩ አማጦ የመጠቀም ፍላጎቱ ከፍተኛ ነው። ፋብሪካዎቹን ወደግል የማዞሩ ሂደት ሙሉ ለሙሉ ሲሳካ የስኳር አገዳ ምርትን በተገቢው ወቅትና ሰዓት በመጠቀም ውጤታማነቱ ስራ ለማከናወን የሚያስችል ዕድሉ ከፍ ይላል ብለዋል። በተጨማሪም የፋብሪካዎቹ የመስፋፋት ዕድላቸውም ከፍ ስለሚል የስራ እድል ለመፍጠር ጉልህ ሚና አለው ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ዶክተር ዳዊት ገለጻ ፋብሪካዎቹ ወደ ግል በሚዛወሩበት ወቅት መንግሥትም የራሱን ካፒታል እንዳያጣ ፤ የግሉም ባለሀብት እንዳይከስር ያሉት ሀብቶች በትክክል ተቆጥረው ካለው የገበያ ሁኔታ ጋር ታይቶ የዝውውር ሂደቱ መደረግ አለበት።



ዶክተር ዳዊት አዬሶ



ዶክተር ጀማል መሀመድ

የአገር ውስጥ ባለሀብት ከሆኑ የባለቤትነት ስሜቱ የበለጠ ስለሚሆን በጨረታ ሂደቱ ላይ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የሚበረታቱበት መንገድ መኖር አለበት። በተጨማሪም ስራ አጥነት እንዳይስፋፋ በነባሩ ፋብሪካዎች ሲሰሩ የነበሩት ሰራተኞች ከአዲስ ባለቤቶች ጋር እንዲሰሩ መደረግ አለበት ሲሉ ገልጸዋል።

በፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የኢኮኖሚ ተመራማሪ ዶክተር ጀማል መሀመድ፤ በበኩላቸው እንደገለጹት ስኳር ፋብሪካዎች ወደግል ዘርፍ መዞራቸው የነበረውን ቀልጣፋ ያልሆነ የአሰራር ሂደት ቀልጣፋ ያደርገዋል።

በሁለተኛው ጂዲፒ ከዚህ በፊት የነበረው የሥነምጣኔ አሰራር በዙም ውጤታማ ባለመሆኑ መንግሥት ኢንዱስትራላይዜሽን ለመጠቀም የወሰነ ሲሆን ያንንም መምራት ከሚችሉት የኢኮኖሚ ዘርፎች አንዱ የስኳር ፋብሪካዎች ናቸው ሲሉ አስረድተዋል።


ፋብሪካዎቹ በመንግሥት አስተዳደር ሲሆኑ የሕዝብን ሀብት ለመጠበቅ ሲባል ውሳኔ ለመስጠት በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች መወሰን ይኖርባቸዋል። ይህም የአሰራር ሂደቱን ዘገምተኛ በማድረጉ የምርት እጥረት እንዲኖር እና የስኳር ዋጋ ንረት እንዲፈጠር አድርጓል ሲሉ ተናግረዋል።

በንግድ ሥርዓት ነገሮች እየታዩ አዋጭ የሆኑ መንገዶች በፍጥነት መቀየር ካልተቻለ አዳዲስ ነገሮች ይፈጠራሉ ያሉት ዶክተር ጀማል፤ ወደግል በሚዞሩበት ወቅት የፋብሪካው ባለቤት እንደየአስፈላጊነቱ አትራፊ የሚያደርገውን ውሳኔ ስለሚወስን የአሰራር ሂደቱ የተቀላጠፈ ይሆናል በማለት ገልጸዋል።

ከአትራፊነት አንጻርም ሲታይም መንግሥት የሚሰራው ለሕዝብ በመሆኑ ኪሳራውም ሆነ ትርፉ ለሕዝብ ነው። ስለዚህ እያንዳንዱን ውሳኔ የሚያስተላልፈው አካል በግለሰብ ደረጃ ተጎጂ ስለማይሆንና የአሰራር ሂደቱ መጓተት ስለሚኖር ትርፋማነቱም አመርቂ አይደለም ብለዋል።

ዶክተር ጀማል እንደተናገሩት የስኳር ፋብሪካዎቹ ወደግል መዞራቸው በለሀብቶቹ በተወዳዳሪነት መንፈስ አስፈላጊውን ቴክኖሎጂ፣ ብቁ የሆነ የሰው ኃይልን ተለዋዋጭ በሆነ መልኩ ለመግዛት እና ለመቅጠር ያስችለዋል።

ወደ ስራ ሲገቡ አመራረቱ ላይ የነበረውን ችግር አጥንተው ያሉትን ችግሮች በመቅረፍ በቂ ስኳር ማምረት ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርባቸዋል ሲሉም መክረዋል።





# በአማራ ክልል በዝናብ መቆራረጥ የዘገየውን የበልግ እርሻ ለማካካስ እየተሠራ ነው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በዝናብ መቆራረጥ ምክንያት የዘገየውን የበልግ እርሻ ሥራ ለማካካስ እየተሠራ ነው።

የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ሰብል ልማት ዳይሬክተር አቶ አግደው ሞላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ በበልግ እርሻ 218 ሺህ 286 ሄክታር በሰብል ለመሸፈን አቅዶ እየሠራ ሲሆን እስከ አሁን መሸፈን የተቻለው 59 ሺህ 889 ሄክታር ብቻ ነው። ይህም የዕቅዱን 27 በመቶ ነው።

የበልግ እርሻ ዝናብ ተጠብቆ የሚሠራ ነው ያሉት አቶ አግደው፤ በዕቅድ ተይዞ የነበረውን ቁጥር እንዳናሳካ ያደረገው ዋነኛ ምክንያት የዝናብ መቆራረጥ ነው። ባለፈው ዓመትም በዚሁ ምክንያት በክልሉ የበልግ እርሻ አልተከናወነም ብለዋል።

የበልግ አምራች አካባቢዎች የእርሻ ዝግጅቱን በጥሩ ሁኔታ የጀመሩ ቢሆንም የነበረው የዝናቡ መቆራረጥ ግን ወደ ኋላ ጎትቷቸው ነበር። አሁን ግን በክልሉ የተሻለ አፈጻጸም እንዲኖር በርብርብ እየተሠራ እንደሆነ ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

በክልሉ አምስት ዞኖች የበልግ እርሻ ተጠቃሚ ናቸው ያሉት አቶ አግደው፤ አሁን ላይ ዝናቡ ጥሩ ሁኔታ ላይ ስለሚገኝ ቀድሞ ለተዘሩ ሰብሎችም ይሁን አሁን በዘር ላልተሸፈኑ መሬቶች ጥሩ አዝማሚያ ታይቷል ነው ያሉት።

በክልል ደረጃ ለበልግ ልማት የሚሆን ሰባት ሺህ 717 ኩንታል ኤምዲኤስ የአፈር ማዳበሪያ ፣288 ኩንታል ዩሪያ ቀርቦ ሥራ ላይ መዋሉን አብራርተዋል። አርሶ አደሩ ያለውን ዝናብ ተጠቅሞ በሰብል ያልተሸፈኑ ቦታዎችን ፈጥኖ ዘር መዝራት እና ቀድሞ የዘራውን የመንከባከብ ሥራ መሥራት ይኖርበታል ሲሉ አሳስበዋል።

በተጨማሪም ውሃ የመያዝ ሥራ ትኩረት ተደርጎ እንዲሠራ ሁሉም ግብርና መዋቅርና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የበልግ እርሻ ልማቱን ስኬታማ ለማድረግ መረባረብ አለባቸው ሲሉ አቶ አግደው መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# በአዲስ አበባ ከ75 ሺህ በላይ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎችን ሚኒስትሪ ለማስፈተን ዝግጅት ተደርጓል

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- ዘንድሮ ለመጀመሪያ ጊዜ በሚሰጠውን የስድስተኛ ክፍል የሚኒስትሪ ፈተና ተማሪዎችን ለማስፈተን የዝግጅት ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የፈተና ዝግጅት እና አስተዳደር ዳይሬክተር አቶ ዲናኦል ጫላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ ከተማ በግል እና በመንግሥት ትምህርት ቤቶች በትምህርት ገበታ ላይ የሚገኙ ከ75 ሺ በላይ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎችን ለማስፈተን ዝግጅት እየተደረገ ነው። ከቢሮ እስከ ትምህርት ቤቶች ድረስ ተማሪዎቹን ለፈተና የማዘጋጀት ሥራ እየተሠራ ይገኛል።

ተማሪዎች የሚኒስትሪ ፈተና ከመፈተናቸው አስቀድሞ የተለያዩ ደረጃቸውን የጠበቁ ሞዴል ፈተናዎችን በማዘጋጀት በወሩ እንዲወስዱ መደረጉን ገልጸው፤ ለፈተናው የተለያዩ አጋዥ መጽሐፍትን አንብበው እንዲዘጋጁ እና እንዲፈተኑ እያደረግን ነው ብለዋል።

በአማርኛ ቋንቋ የሚፈተኑ አራት እንዲሁም በአፋን ኦሮሞ የሚፈተኑ አምስት የትምህርት ዓይነት ፈተናዎች የሚወስዱ መሆኑን አመልክተው፤ በዚህ መሠረትም የሒሳብ፣ የአካባቢ ሳይንስ፣ አማርኛ፣ ኦሮሚኛ እና እንግሊዝኛ የትምህርት ዓይነቶች እንደሚሰጡና እነዚህን ታሳቢ በማድረግ ተማሪዎችን ለፈተና ዝግጁ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ምዝገባው የሚካሄደው በኦንላይን ሲሆን የተመዘገቡ ተማሪዎች የተመዘገቡበትን የስም እና ዕድሜ ስህተት እንዳይኖር ማረጋገጥ እና ማስተካከል ይችላሉ ሲሉ አቶ ዲናኦል አስረድተዋል።

ቢሮው በየክላስተሩ ላሉ ትምህርት ቤቶች ወጥ በሆነ መልኩ ስልጠና በመስጠት ትምህርት ቤቶች ራሳቸው ፈተናዎችን እንዲያወጡ እና እንዲፈተኑ ያደርጋል ነው ያሉት አቶ ዲናኦል፤ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የማጠናከሪያ ትምህርት እንዲሰጥ እና ተማሪዎች እራሳቸውን እንዲያበቁ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ እንደሆነ ገልጸዋል።

እንደ አቶ ዲናኦል ገለጻ፤ በአዲሱ ሥርዓት ትምህርት በየምዕራፉ ማጠናቀቂያ ላይ ለተማሪዎች ፈተና ይሰጣል። ለዚህም አንደኛ ምዕራፍ የሚባለው ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ያለው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ሲሆን ሁለተኛ ምዕራፍ የሚባለው ከሰባት እስከ ስምንተኛ ክፍል ነው። ይህም ተማሪዎቹ በየምዕራፉ ምን ያህል አውቀዋል የሚለውን የምንመዝንበት እና ለቀጣይ የትምህርት ደረጃ ብቁ መሆናቸውን የምንለይበት ነው።

የመጀመሪያ ምዕራፍ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የሚያጠናቅቁት ስድስተኛ ክፍል ላይ ስለሆነ የሚኒስትሪ ፈተናው ተማሪዎች ከታች ጀምረው ራሳቸውን እያነጹ እንዲመጡ የሚያደርግ መሆኑን አመልክተው፤ የትምህርት ጥራትን ከማረጋገጥ አንጻር ከፍተኛ ጥቅም አለው ሲሉ አቶ ዲናኦል ተናግረዋል።

የመማሪያ መጽሐፍት በሚፈለገው ልክ ሀገር ውስጥ አለመገኘት እና በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት ከውጭ የሚመጡ መጽሐፍት የመዘግየት ሁኔታ መኖሩን ጠቁመው፤ የሚኒስትሪ ፈተና የሚሰጥበት ቀናት የሚወሰነው በአገር አቀፍ ደረጃ ቢሆንም እንደ ቢሮ ከሰኔ አጋማሽ በኋላ ለመስጠት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸው፤ ተማሪዎች ለፈተናው ራሳቸውን ዝግጁ እንዲያደርጉ አሳስበዋል።

ዜና



አቶ አብዲ ፍቃዱ



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

አቶ ተስፋዬ ተሰማ



ወይዘሪት ሜሪ ኤፍሬም

# «ከተማችንን ለማሳደግ ግብርን በታማኝነት መክፈል ይገባል»

*- ታማኝ ግብር ከፋዮች*

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ብሎም በአዲስ አበባ ከተማ መሠረተ ልማቶችን የተሟላ ለማድረግና ለማዘመን ግብርን በታማኝነት እና በወቅቱ መክፈል ወሳኝ መሆኑን በአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የእውቅና ሽልማት የተበረከተላቸው ታማኝ ግብር ከፋዮች ተናገሩ።

የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ በ2014 በጀት ዓመት ለ300 የደረጃ ‹ሀ› እና ደረጃ ‹ለ› ግብር ከፋዮች እውቅና ሰጥቷል። እውቅና ከተሰጣቸው ታማኝ ግብር ከፋዮች ውስጥ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ላይ የተሠማሩትና 28 ሚሊዮን ብር ግብር የከፈሉት አቶ አብዲ ፍቃዱ እንደገለጹት፤ ግብር ለሀገር እንዲሁም ለከተማ የኢኮኖሚያዊ እድገት ከማረጋገጥ በሻገር አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማት እንዲስፋፉ ያስችላል።

የሚከፈለው ግብር የሚውለው ለከተማዋ ለውሃና ኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት፣ የመንገድ፣የትምህርት ቤት፣ የጤና ተቋማትና የመሳሰሉት ግንባታ የሚውል ነው። አንድ ሰው አገልግሎት የማግኘት መብቱን ለመጠየቅ ግብር የመክፈል ግዴታውን በኃላፊነት መወጣት አለበት ብለዋል።

አቶ አብዲ ዘንድሮ ለሁለተኛ ጊዜ እውቅና እንደተበረከተላቸው ጠቁመው፤ የተደረገው የእውቅና መርሐ ግብር ለሀገሪቱ እድገት በአግባቡ ኃላፊነታቸውን ለተወጡ ግብር ከፋዮች የሚያበረታታና ሌሎች ግብር ከፋዮች ግብራቸውን በሐቀኝነት እንዲከፍሉ እና የዜግነት ግዴታቸውን እንዲወጡ ያነሳሳል ሲሉ ገልጸዋል።

ሌላው በኬሚካል ማምረት ላይ የተሠማሩትና ከ58 ሚሊዮን ብር በላይ ግብር በመክፈል የእውቅና ተሸላሚ የሆኑት ወይዘሪት ሜሪ ኤፍሬም እንደተናገሩት፤ ግብር ለሕዝቡ መሠረታዊ መሠረተ ልማቶችን ለማሟላት የሚውል ነው። ግብርን በአግባቡ መክፈል መንግሥታዊ አገልግሎቶች የመጠቀም መብት በተሟላ መልኩ ማግኘት ያስችላል።

መንግሥት አቅም ከሌለው የመሠረተ ልማት ሥራ ሊያከናውን አይችልም። ለዚህም ግብር የሚሰውሩ እና የሚያጭበረብሩ አካላት ራስን ማታለል መሆኑን ተገንዝበው ከእኩይ ድርጊታቸው መቆጠብ እና ለግብር ሕጉ ታማኝ መሆን አለባቸው ነው ያሉት።

የእውቅና ሥነሥርዓቱ ግብር ከፋዩን ማኅበረሰብ የሚያበረታታ እና የሚያነሳሳ ነው ያሉት የቺቫ ትምህርት ቤት ተወካይ አቶ ተስፋዬ ተሰማ፤ ትምህርት ቤቱ በ2014 ዓ.ም አንድ ሚሊዮን ብር ግብር ከፍሏል። ምክንያቱም ሀገርን የምንገነባው የሚጠበቅብንን ግብር በሐቀኝነት በመክፈል ነውና ብለዋል።

ግብር ለሃገር ሁለንተናዊ ዕድገት ያለውን ትልቅ ፋይዳ በመረዳት የንግዱ ማኅበረሰብ ትክክለኛውን ግብር በፍቃደኝነት ወቅቱን ጠብቆ በመክፍል ኃላፊነቱን መወጣት አለበት። ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማፋጠንና የመሠረተ ልማቶችን ለማሟላት ግብር መክፈል የንግዱ ማኅበረሰብ ግዴታ ነው ብለዋል።

አሁን ላይ እየተሠሩ ያሉ የመሠረተ ልማት ሥራዎች እንዲስፋፉና እንዲፋጠኑ ሁሉም የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት አለበት ሲሉም ታማኝ ግብር ከፋዮቹ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ደረቅ ቆሻሻን ጥቅም ላይ በማዋሉ ሥራ ከ16 ሺህ በላይ ዜጎች እየተሳተፉ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- በመዲናችን አዲስ አበባ ከ16 ሺህ በላይ ዜጎች በደረቅ ቆሻሻ ሽያጭና ተያያዥ ሥራዎች እንደሚተዳደሩ የአዲስ አበባ ከተማ ፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ ፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የመልሶ መጠቀምና ዑደት ዳይሬክተር አቶ ካሳሁን ፀጋዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በአዲስ አበባ ከተማ ከ16 ሺህ በላይ ዜጎች በማኅበር ተደራጅተው ቆሻሻን ከተለያዩ ስፍራዎች ሰብስበው በመሸጥ ላይ ናቸው።

እንደ አቶ ካሳሁን ገለፃ፤ በየመንደሩ ተጠራቅሞ የሚገኘውን ደረቅ ቆሻሻ በመሰብስብ መልሶ ለአገልግሎት እንዲውል የሚረዳ ሥራ የሚያከናውኑ ዜጎች የአካባቢ ብክለትን ከመከላከል ባለፈ የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ገቢ በማሳደግ ሕይወታቸውን በተሻለ መንገድ መምራት ችለዋል።

ከዚህ ባለፈ 40 የፅዳት ድርጅቶች የየራሳቸውን ተሽከርካሪዎች በመጠቀም ደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ ሥራ ላይ እየተሳተፉ መሆኑንም አስታውቀዋል። መልሶ ጥቅም ላይ የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን የመለየት ሥራ የሚያከናውኑ ማኅበራት ከ10 ዓመት በፊት የደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ ሥራ ላይ ተደራጅተው ወደ ሥራ መግባታቸውን አስታውሰዋል።

ሥራውን በጀመሩበት ወቅት ቆሻሻውን ሰብስበው የሚገፉበትን ጋሪ መግዣ በማጣት በጀርባቸውና በጭንቅላታቸው ያጓጉዙ እንደነበር የገለጹት አቶ ካሳሁን፤ አሁን ላይ ግን የራሳቸውን የጭነት ተሽከርካሪ መግዛት የቻሉ ማኅበራት መኖራቸውንም ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ካሳሁን ገለፃ፤ ዛሬ ላይ በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ ሥራ የተሰማሩ ማኅበራት ከ120 በላይ የጭነት ተሽከርካሪዎች ባለቤት ናቸው። በተጨማሪ ለሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ የበኩላቸውን ሚና በመወጣት በትጋት እየሠሩ ይገኛሉ።

የከተማ አስተዳደሩ ከማኅበራቱ ጎን በመሆን የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እያደረገላቸው ነው ያሉት አቶ ካሳሁን፤ ቆሻሻ ተሰብስቦ ወደ ማስወገጃ ጣቢያ ከሄደ በኋላ በሰበሰቡት ቆሻሻ መጠን ክፍያ እንደሚሰጣቸው ገልጸዋል።

ኤጀንሲው በዋናነት ደረቅ ቆሻሻን በማስተዳደር ፕላስቲኮች፣ ወረቀት፣ ብረታ ብረት፣ ጠርሙስና የጨርቃ ጨርቅ ምርቶች መልሰው ጥቅም ላይ እንዲውሉ እየሠራ ነው ያሉት አቶ ካሳሁን፤ በመዲናዋ ከሚሰበሰበው ደረቅ ቆሻሻ ውስጥ መልሶ ጥቅም የሚውለው 18 በመቶው ያህሉ ብቻ መሆኑን አስታውቀዋል።

ቆሻሻ በአግባቡ ካልተያዘ የበሽታ ምንጭ በመሆን አየርን፣ አፈርን፣ ውሃን ይበክላል በዕፅዋት፣ በሰውና በእንስሳት ጤና እንዲሁም በግብርናው ዘርፍም የመሬት ለምነትን በመቀነስ ጉዳት እንደሚያስከትልም ገልጸዋል። የከተማ ውበትን በመቀነስና የአካባቢ ሥነምሕዳርን በማበላሸት በቱሪዝም ዘርፉ ላይም ጫና እንደሚያሳድር ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ በደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ላይ መሻሻል ቢታይም አሁንም የማኅበረሰቡ ተሳትፎ አነስተኛ በመሆኑ ኤጀንሲው የቤት ለቤት ግንዛቤ ሰጪ ባለሙያዎችን በመመደብ ዜጎች ቆሻሻን እንዴት ማስወገድና መለየት እንዳለባቸው እያስተማረ ይገኛል ብለዋል።

በተጨማሪም በደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ላይ ያተኮሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በቋሚነት በማዘጋጀት ሳምንታዊ የንቅናቄ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን አቶ ካሳሁን አስታውቀዋል።

# በመዲናዋ የጎርፍ አደጋን ለመከላከል በቅንጅት እየተሠራ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ በበልግና በክረምት ወቅት የሚከሰተውን የጎርፍ አደጋ አስቀድሞ ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ ነው ሲል የአዲስ አበባ የእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ የእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ አቶ ንጋቱ ማሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመዲናዋ በበልግና በክረምት የሚደርሰውን የጎርፍ አደጋ አስቀድሞ ለመከላከል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ትኩረት ተሰጥቶ ሲሠራበት ቆይቷል። አደጋውንም ለመከላከል በከተማ ደረጃ የእሳትና አደጋ ስጋት ኮሚሽን የአሰሳ ጥናት ተሠርቶ ለሚመለከታቸው አካላት የመፍትሔ ምላሽ እንዲሰጡበት አሳውቋል።

በአዲስ አበባ ከተማ በአሥራ አንዱም ክፍለ ከተሞች በበልግና በክረምት ወቅት የሚደርሰውን የጎርፍ አደጋን ለመከላከል ኮሚሽኑ ከመንገዶች ባለስልጣን፣ ከአካባቢ ጥበቃና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እየሠራ ነው ብለዋል።

በተጨማሪም በወንዝ ዳርቻዎች አካባቢ የጎርፍን አደጋን ለመከላከል የድጋፍ ግንብና የመሳሰሉ የመከላከያ ሥራዎች መሠራት አለባቸው የሚል ሀሳብ በኮሚሽን መሥሪያ ቤቱ በኩል ሀሳብ ቀርቦ አደጋውን ለመከላከል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ የገለጹት አቶ ንጋቱ፤ በመዲናዋ ተዳፋታማ እና በወንዝ ዳርቻዎች አካባቢ የሚኖሩ ዜጎችን ከጎርፍ አደጋ ለመከላከል የተለያዩ ሥራዎች ስለመሠራታቸው ተናግረዋል።

የበልግ ዝናብ ብዙ የማይቆይ ቢሆንም በመዲናዋ ባሳለፍነው ቅዳሜ ዕለት በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ አሥራ ሁለት በተለምዶ ማንጎ ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በደረሰው የበልግ ጎርፍ አደጋ የአራት ሰዎች ሕይወት ማለፉንና ከአምስት እስከ ስድስት ሚሊዮን ብር የሚገመት ንብረት መውደሙን አስታውሰው፤ በበልግ ዝናብ የሚደርሰውን የጎርፍ አደጋ ለመከላከል የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም አደጋውን ለመከላከል ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

በቀጣይ ክረምት ሊከሰት የሚችለውን የጎርፍ አደጋ ለመከላከል በትብብርና በቅንጅት መሥራት ተገቢ ነው ሲሉ አመልክተዋል።

በወንዝ ዳርቻዎች አካባቢ መኖሪያቸውን ያደረጉና በተዳፋት የመሬት አቀማመጥ የሚኖሩ የመዲናዋ ዜጎች ከጎርፍ አደጋ ራሳቸውን ለመከላከል ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው ጠቁመው፤ ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎችን የሚያስተዳድሩ የመንግሥት አካላት ማኅበረሰቡን ከጎርፍ አደጋ ለመከላከል ኮሚሽኑ የሚያደርገውን ጥረት መደገፍና በቅንጅት መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

በተደጋጋሚ ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ የሆኑ የመዲናዋ ኗሪዎች የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸውና በመገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ መልዕክቶችን መከታተል እንደሚገባቸው ጠቁመዋል።

# ከሰላም ስምምነቱ በኋላ ሀገራት ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸው የልማት ትብብር ጨምሯል

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ መንግሥት እና በሕወሓት መካከል የተፈረመውን የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት ተከትሎ ሃገራት ከኢትዮጵያ ጋር የኢኮኖሚ ትብብር ማደስ መጀመራቸውን የገንዘብ ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት በገንዘብ ሚኒስቴር የመንግሥታት ትብብር ዳይሬክተር አቶ ደጀኔ ግርማ እንደተናገሩት፤ የተፈረመውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በኢትዮጵያ እና በሌሎች ሀገራት መካከል ተቋርጠው የነበሩ የልማት ትብብሮች አሁን ላይ በስፋት እየተመለሱ መምጣታቸውን ተናግረዋል፡፡

በርካታ ሀገራት የልማት ትብብራቸውን ለመቀጠል ያላቸውን ፍላጎት ከማሳየታቸውም በላይ የሚያደርጉትን የገንዘብ ድጋፍ አጠናክረው መቀጠላቸውን የተናገሩት አቶ ደጀኔ፤ የፈረንሳይ፣ የጀርመን፣ የፊንላንድ፣ የስፔን እና የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በሃገሪቱ ጉብኝት ማድረጋቸውን ገልጸው ልማታዊ ድጋፍ ለማድረግም ስምምነት መፈራረማቸውን አስረድተዋል።



አቶ ደጀኔ ግርማ

ስፔን የልማት ትብብር ማዕቀፉን ለማደስ ዝግጁ መሆኗን ያነሱት የመንግሥታት ትብብር ዳይሬክተሩ፤ ሀገሪቷ 44 ሚሊዮን ዩሮ ለመስጠት ቃል ገብታለች ነው ያሉት።

አቶ ደጀኔ አያይዘውም፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የልማት ድጋፉን ለማጠናከር በርካታ ዲፕሎማሲያዊ ተግባራትን ሲያደርግ መቆየቱንም ጠቁመዋል። ለዚህም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ውይይት ሲደረግ መቆየቱንና ከተለያዩ ሀገራት ኤምባሲዎች ጋር የሰላም ስምምነቱን በተመለከተ ውይይት ሲያደርግ ቆይቷል ብለዋል።

ሀገራቱ ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸው ግንኙነት መሻሻሉን መሠረት በማድረግ በኢትዮጵያ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ሲያጋጥሙ የሚፈለገውን የመልሶ ግንባታና የማገገሚያ ድጋፍን በተመለከተ ውይይቶችን አድርገናል ያሉት የመንግሥታት ትብብር ዳይሬክተሩ ገንዘብ ሚኒስቴር ስለሀገራዊ ልማቶች ለልማት አጋሮቻችን ግንዛቤ ለማስጨበጥ ጥረት እያደረገ መሆኑንም አስረድተዋል።

የቀድሞ የልማት ትብብር አጋሮች የሚያደርጉትን ድጋፍ ለማስቀጠል ከሚደረገው ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ጎን ለጎን አዳዲስ የልማት አጋሮችን በመሳብ ረገድ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚቻለውን ሁሉ ጥረት እያደረገ መሆኑንም አስረድተዋል።

# ሕወሓት ከሽብርተኝነት መዝገብ መነሳቱ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በሕወሓት ላይ የተጣለውን የሽብርተኝነት ስያሜ በምክር ቤቱ እንዲነሳ ሁኔታዎችን እንደሚያመቻች ተገልጿል። በትግራይ ሕጋዊ ያልሆነው የክልል መንግሥት ሲፈርስ ደግሞ በሕጋዊ አስተዳደር መተካት እንዳለበት ማወቅ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

በትግራይ ሕጋዊ ምርጫ ተካሂዶ መደበኛ አስተዳደር እስኪቋቋም ድረስ ደግሞ በጊዜያዊነት እንዲሠራ በቀረበ አስተዳደር ውስጥ ደግሞ ሕወሓትም አለበት። በመሆኑም በምክር ቤቱ ከዚህ ቀደም ሕወሓት ላይ የተወሰነውን የሽብርተኝነት ውሳኔ ማንሳቱ የሰላም ስምምነቱ ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲፈጸም ይረዳል ብለዋል።

በተጨማሪ ሽብርተኝነቱን ማንሳቱ ለትግራይ ሕዝብ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማቅረብና የበጀት ድጎማውን ለአካታች ጊዜያዊ አስተዳደሩ ለማቅረብ የሚያግዝ መሆኑን ሚኒስትሩ ጠቁመዋል።

ሚኒስትሩ እንዳስታወቁት፤ ሕወሓት ከሽብርተኝነት ሲነሳ የሰላም ስምምነቱ ተተግብሮ አብቅቷል ማለት አይደለም። ከዚህ ጎን ለጎን በተቋቋመው የተሐድሶ ኮሚሽን አማካኝነት የሕወሓትን ታጣቂዎች አነስተኛ መሣሪያዎች ርክክብ በማድረግ ወደ ካምፕ እንዲገቡና የተለያዩ የተሐድሶ ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ ይደረጋል።

የተቋቋመው የተሐድሶ ኮሚሽን በአሁኑ ወቅት ሃብት በማሰባሰብ ላይ መሆኑን ጠቁመው፤ ኮሚሽኑ ቀሪ ሥራዎቹን በማከናወን የሰላም ስምምነቱ በይበልጥ ተግባራዊ ሆኖ እንደሚቀጥል አብራርተዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ ቤልጂጌ ባቀረቡት የውሳኔ ሃሳብ መሠረት፤ ሕወሓት አጠቃላይ ተግባሩ የሽብር ስለነበር ምክር ቤቱ በሽብርተኝነት እንዲፈረጅ ወስኖ እንደነበር አስታውሰዋል። በፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት የሕወሓት ኢ-ሕገመንግሥታዊ እንቅስቃሴ እንዲቀለበስ መደረጉን ጠቁመው፤ ስምምነቱን ተከትሎ አሁን ላይ ሕወሓትን ከሽብርተኝነት ማንሳቱ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን ይረዳል ሲሉ ተናግረዋል።

ሕወሓትን ከሽብርተኝነት ለማንሳት የቀረበው የውሳኔ ሃሳብ የሰላም ስምምነቱ አፈጻጸም በበለጠ ውጤታማ እንዲሆንና የፖለቲካ ልዩነቶችን በሰለጠነ መንገድ ለመፍታት የሚረዳ ነው ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ ለሰላም ቀጠሮ መስጠት አይገባም፤ የሠላም ጊዜው አሁን ነው ብለዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ የደህንነት አማካሪ ሚኒስትር አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን በበኩላቸው፤ አሁን ላይ በትግራይ የተለያዩ ፓርቲዎችን ያካተተ የጊዜያዊ አስተዳደር አባላት ተለይተው ዝርዝሩ ይሁንታ እንዲያገኝ ለፌዴራል መንግሥት መላኩን ጠቁመዋል። ሕወሓት ከቀድሞው የሽብር ተግባር ወደ ሰላም ከተመለሰ ለትግራይ ሕዝብም አማራጭ መስጠትና ችግሮችን በሰላም መፍታት ይገባል ሲሉም ተናግረዋል።

በሌላ በኩል የሽብርተኝነት ውሳኔው ቢነሳ ሕወሓት ዳግም ጦርነት እንደማይከፍት ምን ዋስትና አለ የሚል ስጋት ላላቸው አካላት መከላከያ ሠራዊት ሀገር የመጠበቅ ኃላፊነቱን በማንኛውም ሰዓት እየፈጸመ በመሆኑ ምንም ስጋት ሊያድርባቸው አይገባም ብለዋል።

የምክር ቤት አባላት በበኩላቸው፤ በሰላም ስምምነቱ መሠረት ሕወሓት ትጥቅ የፈታበት መንገድና አፈጻጸሙን በተመለከተ በዝርዝር ሪፖርት ለምክር ቤት አባላት ሳይቀርብ የሽብርተኝነት ውሳኔውን ለማንሳት ውይይት ማድረግ ተገቢ አይደለም፤ በመሆኑም በቀጣይ ጉዳዩ መታየት ነበረበት የሚል ሃሳብ አንስተዋል።

ሌሎች የምክር ቤት አባላት ደግሞ፤ ለዘላቂ ሰላም ሲባል በደሎችን ትቶ ወደ እርቅና አንድነት ለመምጣት ሕወሓትን ከሽብር የማንሳት ጊዜው አሁን ነው ሲሉ አስተያየት ሰጥተዋል።

በፕሪቶርያው ስምምነት አንቀጽ 10/1 መሰረት የሕዝብ ተወካዮችና የትግራይ ክልል ምክር ቤት ምርጫ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አማካኝነት እስኪከናወን ድረስ አካታች ጊዜያዊ መንግሥት እንደሚመሠረት ተገልጿል።

ምክር ቤቱ ሚያዚያ 28 ቀን 2013 ዓ.ም ባካሄደው 6ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 13ኛ መደበኛ ስብሰባው ላይ ሕወሓትን አሸባሪ ብሎ መሠየሙ የሚታወስ ሲሆን የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት በአንደኛ ልዩ ስብሰባው ሕወሓትን ከሽብር ስያሜ ለማስነሳት የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ በ61 ተቃውሞ በ5 ድምፀ ተዓቅቦ በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል።

# «ጊዜው የትግራይን ልማትና መልሶ ግንባታ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

በድብብቆሽና በሥልጣን ሽሚያ ውስጥ ከተዘፈቅን የገጠመን ችግርና ውጥረት የማይራዘምበት ምክንያት አይኖርም ያሉት ሚኒስትሩ፤የተጠላለፈ ችግራችን መፍትሔ እንዲያገኝ ዕይታችንን ወደ ልማትና ዕድገት በማዞር፤ የሕዝባችንን ወቅታዊ ሁኔታ የሚረዳ፣ በአስተውሎት የሚመራ፣ ኃላፊነት የሚሰማው አመራር መፍጠር አለብን ሲሉ አስገንዝበዋል። በአንድነት ሆነን ሌሎች ሕዝቦች እና ኃይሎችን ከጎናችን በማሰለፍ አሁናዊ መፍትሔ ላይ ትኩረት አድርገን እንረባረብ ሲሉም አሳስበዋል።

ይህ ጊዜ ሀገራችንንና ሕዝባችንን የምናድንበት፣ የሕዝባችንን ብሩህ ተስፋ የምናረጋግጥበት፣ የትግራይ ልማትና መልሶ ግንባታ የምናበስርበት ጊዜ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ሕዝባችንን በቅንነት የሚያገለግሉ ጠንካራ ሰዎች እንዲኖሩን ማድረግ ይገባል እንጂ፣ ሥልጣን የምንሻማበት፣ የፓርቲዎች ፖለቲካዊ አጀንዳ የምናስቀድምበትና የምንፋጠጥበት ጊዜ አይደለም ሲሉ ጠቁመዋል።

ጊዜው የተጋሩን ጥንካሬ የሚፈልግ፣ እይታውና ጉዳዩ ሰላም፣ ትግራይ እና የትግራይ ሕዝብ መልሶ ለማቋቋምና የተጎዱ መሠረተ ልማቶችን መልሶ ለመገንባት ትኩረት የሚሰጥ አስተዋይ መሪ የሚጠይቅበት መሆኑን ጠቁመው፣ ቀጣዩ ጊዜ ዴሞክራሲያዊ አመራር የማይታፈንበት፣ የሃሳብ ልዩነት የሚከበርበት፣ ነፃ እና ፍትሐዊ ምርጫ ለማካሄድ የተመቻቸ ሁኔታ የምንፈጥርበት ወቅት ነው ብለዋል።

የጊዜያዊ አስተዳደር መሪነት መውሰድ ማለት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የግለሰቦች ሥራ አስፈፃሚ መሆን አይደለም ያሉት ዶክተር አብርሃም፤ ይልቁንስ ሕዝባችን ወደ ተሻለ ኑሮ የሚመለስበት የግልና የመንግሥት አገልግሎቶች በሙሉ እንዲጀመሩ የሚያደርግ፣ የትግራይ መልሶ ማልማት ወደ ተግባር የሚለውጥ፣ ከሁሉም አቅጣጫ የተፈናቀሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ የሚያደርግና ለተጎዱት ወገኖች ተገቢ ሥልጠና እና ድጋፍ በመስጠት ወደ ተሻለ ኑሮ ማስገባት የሁሉም ኃላፊነት እንደሆነ በትኩረት መረዳት ያስፈልጋል ሲሉ አሳስበዋል።

## በክልሉ በድርቅ ለተጎዱ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በተከሰተው የዝናብ እጥረት ሳቢያ ድርቅ ተከስቷል። በዚህም የክልሉ መንግሥት በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች ከ105 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት የዓይነት ድጋፍ አቅርቧል።

እንደ አቶ ፋሲካ ገለጻ፤ ደረቃማ በሆኑ በደቡብ ኦሞ፣ በኮንሶ ፣ በጎፋ ዞን ኡባ እና ዛላ ወረዳዎች ፣ በጋሞ ዞን ወረዳዎች፣ በቡርጂ፣ በአማሮ፣ በደራሼ እና በአሌ አካባቢዎች የዝናብ እጥረት በመከሰቱ ማኅበረሰቡ ለችግር ተዳርጓል። በዚህም የክልሉ መንግሥት በሰዎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ክትትል በማድረግ በየጊዜው ድጋፍ በማቅረብ ላይ ይገኛል።

በክልሉ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች 917 ሺህ ዜጎች በፌዴራል የሴፍትኔት ፕሮግራም አማካኝነት ተጠቃሚ ሆነዋል ያሉት አቶ ፋሲካ፤ በተጨማሪ ድርቅ በተከሰተባቸው ስምንት ወረዳዎች ላይ ለ175 ሺህ ዜጎች 144 ሚሊዮን ብር ድጋፍ መደረጉን ገልጸዋል።

የተከሰተው ድርቅ በእንስሳት ላይ የከፋ አደጋ እንዳያስከትል ለእንስሳት መኖ የማቅረብ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል። የክልሉ መንግሥት በአርብቶ አደር አካባቢዎች ሰባት ሚሊዮን ብር ወጪ በማድረግ የእንስሳት መኖ ግዢ ፈጽሟል። የእንስሳት መኖውም ድርቅ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ላይ በመሰራጨት ላይ ነው ብለዋል።

በደቡብ ኦሞ ዞን በስድስት ወረዳዎች ላይ በወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ አማካኝነት 300 ሺህ የሚጠጉ ዜጎች እህል እየቀረበላቸው መሆኑን ጠቅሰው፤ በኮንሶ ዞን ከ200 ሺህ በላይ የሚሆኑ ዜጎች የክልሉ መንግሥት ካደረገው ድጋፍ በተጨማሪ የፌዴራል መንግሥት ድጋፍ በማቅረብ ላይ መሆኑን አስረድተዋል።

በተጨማሪም በቡርጂ፣አማሮ፣በአሌ እና ደራሼ ልዩ ወረዳዎች ላይ ድጋፍ በመደረግ ላይ መሆኑን ገልጸው፤ በክልሉ በሚገኙ 48 ወረዳዎች ከ300 ሺህ በላይ ዜጎች አልሚ ምግብ ቀርቦላቸዋል።

ኮሚሽኑ ተጨማሪ ድጋፎችን ለመፈጸም የሚያስችል 50 ሚሊዮን ብር በላይ ተጨማሪ በጀት መመደቡን በመግለጽ በቀጣይ ችግር ባለባቸው ቦታዎች ላይ ምላሽ በመስጠት እና እህል ማቅረብ የሚያስችል ሥራ በመሥራት ላይ መሆኑን ገልጸዋል።

በድርቅ ምክንያት የተከሰተውን የውሃን እጥረት ለመከላከል 27 የውሃ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ተገዝተው ወደ ሥራ ለማስገባት እንቅስቃሴ ተጀምሯል ሲሉ አቶ ፋሲካ ተናግረዋል።

በሌላ በኩል የወባ ወረርሽኝ ባለባቸው አካባቢዎች ላይ የክልሉ ጤና ቢሮ ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመሆን አጎበር በማቅረብ ላይ መሆኑን ገልጸዋል። በአጭር ጊዜ ተመርተው የሚደርሱ የምግብ አይነቶችን በማልማት የድርቁን ተጽዕኖ ለመቀነስ ጥረት እየተደረገ ነው ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ በተለይ የቦሎቄና የፍራፍሬ ምርጥ ዘሮች በ40 ሚሊዮን ብር ተገዝተው ለአርሶ አደሩ እየተከፋፈሉ መሆኑን አስታውቀዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ የተጀመረውን የሰላም ሂደት ለማሳካት የተወሰደ በጎ ርምጃ ነው!

የለውጥ ኃይሉ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ መንግስት መሆኑን ተከትሎ በአገር ውስጥም ሆነ ውጪ ያሉ አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ በድርድር የሚፈቱበትን አቅጣጫ አስቀምጧል፤ በሮቹን ለውይይትና ለድርድር ክፍት በማድረግም በመተማመን ላይ የተመሰረተ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ረጅም መንገድ ተጉዟል። በዚህም በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍያለ እውቅና ተችሮታል።

በተለይም በአገሪቱ ፖለቲካ ዘመናት ያስቆጠረውን ፤ አገርና ሕዝብን በየዘመኑ ብዙ ዋጋ ያስከፈለውን የሴራ ፖለቲካ በመቀየር፤ በመተማመን ላይ የተመሰረተ አዲስ የፖለቲካ ባህል ለመፍጠር ትልቅ ዕድል ይዞ የመጣ፤ በብዙዎችም ዘንድ ከፍያለ ተስፋ የተጣለበት መሆኑ የሚታወስ ነው።

በመንግስት እና በተቃዋሚ ኃይሎች መካከል ይዘነው የመጣነውን በጠላትነት የመፈራረጅ ባህል በመቀየር ተቃዋሚ ኃይሎች ለአዲሱ የፖለቲካ ዕሳቤ መበልጸግ ተጨማሪ አቅም የሚሆኑበትን የተሻለ እድል ይዞ የመጣ፤ ይህም በአብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደ መልካም ጅማሮ ተቀባይነት አግኝቶ በተወሰነ ደረጃ መተማመን ፈጥሮም ነበር።

በዚህም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በአገር ውስጥ ትልቅ የለውጥ ሀዋርያ ተደርገው የተወሰዱበት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃም የዓለም የሰላም ኖቤል ተሸላሚ የሆኑበት እውነታ ታሪካዊ ክስተት ሆኖ ተመዝግቧል። በዚህም የአገራችን ገጽታ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተሻሻለ የመጣበት ሁኔታም በስፋት ተስተውሏል ።

ይህ ተስፋ ሰጭ እውነታ አገራዊ የፖለቲካ ምህዳሩን እያጠራ ባለበት ሁኔታ ፤ ቁጭ ብሎ መነጋገርን ሆነ ቁጭ ብሎ በመነጋገር ችግሮችን ለማስወገድ የተያዘው የመንግስት የፖለቲካ አቅጣጫ በአንዳንድ ወገኖች ያልተገባ ትርጓሜ በመያዙ፤ አገር ወዳልተገባ ጦርነት ውስጥ ለመግባትና በዚህም ብዙ ዋጋ ለመክፈል ተገዳለች።

በተለይም መንግስት ከሕወሓት ጋር የነበረውን አለመግባባት በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት፤ ከፖለቲካ መስመሩ በተጨማሪ የአገር ሽማግሌዎችንና እናቶችን በመላክ የሄደበት ርቀት የቱን ያህል ለሰላም የነበረውን ቁርጠኝነት በተጨባጭ ያመላከተ ነበር።

ይህም ሆኖ ግን በአሸናፊና ተሸናፊ ትርክት ላይ የተመሰረተው እና ዘመናት ያስቆጠረው አሮጌው የፖለቲካ አስተሳሰብ ባጠላው የጥፋት ጥላ አገርና ሕዝብ ወዳልተፈለገ ጦርነት ገብተው፤ የሽግግር ወቅት ፖለቲካውም ባልተጠበቁ ተግዳሮቶች ለመፈተን ተገዷል።

መንግስት አገርንና ሕዝብን ከየትኞቹም የሽብር ጥቃቶች የመከላከል የህግና የሞራል ኃላፊነት ስለነበረበት፤ በአንድ በኩል በአገር ላይ በግልጽ የታወጀውን ጦርነት እየመከተ፤ በሌላ በኩል ቀድሞ የጀመረው የሰላም ጥረት ፍሬ እንዲያፈራ በኃላፊነት መንገድ ተንቀሳቅሷል።

ብዙ መስዋዕትነት የጠየቀውን ግጭት በዘላቂ የሰላም ስምምነት በመቋጨት ከቀደመው የአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት በመውጣት አገር እንደ አገር አሸናፊ የምትሆንበትን የሰላም ስምምነት በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ከተማ ተፈራርሟል። በዚህም አገራዊ የግጭት አፈታት ስርአታችን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ እንዲገባ አስችሏል።

ትናንት የኢፌዴሪ ተወካዮች ምክር ቤት ሕወሓትን ከሽብርተኝነት መዝገብ የማንሳቱ ውሳኔ የዚሁ የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት አንድ አካል ነው፤ መንግስትም ሆነ ሕወሓት ቀደም ሲል ለተደረሱ ስምምነቶች ተገዥ ስለመሆናቸው እንደ አንድ ማረጋገጫ ተደርጎም የሚወሰድ ነው።

ውሳኔው በጦርነቱ ውድ ዋጋ የከፈሉ የአገራችንን ሕዝቦች በሰላም ለመካስና ከግጭት ይልቅ ለሰላም እና ለሰላም እሴቶች ትኩረት ለመስጠት እንደ ትልቅ አቅም የሚቆጠር ነው።

ከግጭትና ከጦርነት ከሰብአዊ እልቂትና የሀብት ውድመት ውጪ ማንም ተጠቃሚ ሊሆን እንደማይችል፤ ከዚህ ባለፈ በአሸናፊና ተሸናፊ ትርክት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ዕሳቤ አገር እና ሕዝብን ያልተገባ ዋጋ ከማስከፈል ባለፈ የተረጋጋች እና የበለጸገች አገር መፍጠር እንደማያስችል በአግባቡ ለመረዳት የተሻለ አጋጣሚ የሚፈጥርም ነው፡፡ በአጠቃላይ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ የተጀመረውን የሰላም ሂደት ለፍሬ ለማብቃት የተወሰደ በጎ ርምጃ ነው ማለት ይቻላል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ግድቡ ለኢትዮጵያውያን የኃይል እና የይቻላል መንፈስ ምንጭ ነው!

**ትንሳኤ አበራ**

የዓለም አገራት አይናቸውን ኢትዮጵያ ላይ ከተከሉ ቆየት ብለዋል:: ልክ ሰጎን እንቁላል ስትፈለፍል አይኖቿን ከእንቁላሎቿ ላይ እንደማታነሳ ሁሉ የዓለም አገራት አይኖቻቸውን ኢትዮጵያ ላይ ተክለው ማንሳት ካቃታቸው ዓመታት እየተቆጠሩ ነው:: ሰጎንስ ፈልፍላ ስትጨርስ አይኖቿ ከእንቁላሎቿ ላይ ታነሳለች::

እነዚህ አገራት ግን እንኳን አይናቸውን ሊያነሱ ይቅርና ዕለት ተዕለት ስሟን የጣፈጣቸው እስኪመስል ድረስ ሳያነሷት ውሎ ማደር አልሆነላቸውም:: ይህ አልበቃ ብሏቸው በየጉባኤዎቻቸው የኢትዮጵያን ጉዳይ እንደ ራሳቸው ጉዳይ አጀንዳ አድርገውታል::

የኢትዮጵያ ውስጣዊ ሆነ ውጫዊ ጉዳዮች ይመለከተናል የሚሉት የዓለም አገራት በሁሉም ጉዳዮቿ ጣልቃ ከመግባት ባዝነው አያውቁም:: እራሳቸው ፈላጭ ቆራጭ አድርገው ስለሚያዩ የኢትዮጵያን ጉዳይ በእጃቸው አስገብተው እንደፈለጉት ሊያደርጉት እንደሚችሉ ያስባሉ::

የቅርቡን ብናነሳ እንኳን የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታ ምክር ቤት የኢትዮጵያ ጉዳይ ከአስራ ሁለት ጊዜ በላይ አጀንዳ አድርጎ ማቅረቡን እናስታውሳለን:: አሁን ላይ ደግሞ የአረብ ሊግ ምክር ቤት የኢትዮጵያን ጉዳይ ቋሚ አጀንዳ ማድረጉ እየሰማን ነው::

ታዲያ እነዚህ አገራት ምን ፈልገው ይሆን ነጋ ጠባ የኢትዮጵያ ጉዳይ የራሳቸው ጉዳይ እንደሆነ ሁሉ መጨነቅና መጠበባቸው ስንል መጠየቅ ይገባል:: መቼም የሚፈልጉ አንዳች ነገር ከሌላቸው በስተቀር እንዲህ የሙጥኝ የሚሉበት ምክንያት ይኖራቸዋል ብሎ መገመት ይከብዳል ::

ኢትዮጵያን እንዲህ አይን ውስጥ እንድትገባ ያደረጓትን የተለያዩ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል:: ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የአፍሪካ አገራት በቀኝ ግዛት ለመቆጣጠር የነደፉትን ስትራቴጂ በማክሸፍ ብቸኛ አፍሪካዊት ፋና ወጊ አገር መሆኗ ዋንኛው ነው ::

ሌላው ደግሞ አሁን ላይ ኢትዮጵያ የአፍሪካን ጉዳይ በአፍሪካውያንና በአፍሪካ ኅብረት አማካይነት ብቻ ሊታይ ይገባል በሚል የያዘችው ጽኑ አቋም የጎረበጣቸው ለመሆኑ ብዙ ማሳያዎችን ማንሳት ይቻላል::

ይህ የኢትዮጵያ አቋም ደግሞ ዛሬ ላይ ለሚፈልጉት ዘመናዊ ባርነት እንዲመቻቸው የነደፉትን ስትራቴጂ ቀድሞ እያከሸፈባቸው መሆኑ ስለገባቸው እንዳሻቸው እንዳይፈነጩ ማሰሪያ ልጓም ሆኖ መቸገራቸው በምክንያትነት የሚጠቀሱ ናቸው::

ታዲያ በመንገዳቸው ሁሉ እንቅፋት እየሆነች አላማቸውን እንዳይሳካ እያስቸገረቻቸው እንደሆነ የሚገምቱትን ኢትዮጵያን እነሱ ወደ ሚፈልጉት መሥመር እስክትገባ ድረስ በሚችሉት መጠን ለማዳከም ከዚህ የተሻለ ምን ምክንያት ሊኖራቸው አይችልም::

ስለዚህ አቅማቸው የፈቀደውን ሁሉ በማድረግ አማራጭ ይሆናል ብለው ያሰቡትን በውጫዊም ሆነ በውስጣዊ ጉዳዮቿ ጣልቃ ከመግባት ኢትዮጵያን ሰላም መንሳት ከተቻላቸው መበታተንና ማፍረስ በስውር እያሰሩበት ያለ ዓላማ ነው::

ይህንን ዓላማቸው ለማሳካት የማይሞክሩት፤ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም:: በተለይ ኢትዮጵያ የታላቁን ሕዳሴ ግድብ ያለምንም እርዳታ በራሷ ዜጎች አንድነትና ትብብር ለመገንባት መነሳቷ ከእንቅልፋቸው ያባነናቸው ግብጽና ሱዳን የግድቡ ግንባታ እንዳይካሄድ ብዙ ጥረት አድርገዋል::

ሕዳሴውን ግድብ በተመለከተ በሚደረጉ ድርድሮች ላይ አገራቱ በተደጋጋሚ የሀሳብ መዋዥቆችን ከማሳየት ጀምሮ፤ ግንባታውን ዓለም አቀፍ አጀንዳ ለማድረግ ረጅም ርቀት ሄደዋል። አሁን ላይም የአረብ ሊግ በቅርቡ ያወጣው መግለጫ የዚሁ እውነታ ማሳያ ነው ::

የአረብ ሊግ ለየት የሚያደርገው የኢትዮጵያ ግድብ ጉዳይ 140 ሚሊዮን አረብ አገራት ዜጎችን የሚመለከት ጉዳይ አድርገው መውሰዳቸው ነው:: መግለጫ በግልጽ ለግብጽ ያላቸውን ወገንተኝነት የሚያረጋግጥ ነው:: በዚህ ውስጥ እንደተለመደው የግብጽ እጅ ጎላ ብሎ ታይቷል::

የግብጽ አሁናዊ ማስፈራሪያ ‹‹ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ውጭ ታሳደራለች›› አይነት ነው:: የግብጽ አቋም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር እና የአፍሪካ ህብረት ድንጋጌን እንዲሁም ኢትዮጵያን ጨምሮ ግብጽና ሱዳን በግልጽ እ.ኤ.አ መጋቢት 2015 ያደረጉትን ስምምነት የሚጥስ ነው::

ግድቡን በተመለከተ ኢትዮጵያ በያዘችው ጠንካራ አቋም እና በተደጋጋሚ ባሳየችው ቁርጠኝነት ጉዳዩ በአፍሪካ ኅብረት በኩል እንዲታይ ተደርጓል። ይህ እውነታ አፍሪካውያን ችግሮቻችውን በራሳቸው አቅም መፍታት እንደሚችሉ እንደ አንድ ማሳያም ተደርጎ ተወስዷል። ይህ የአፍሪካዊነት ከበሬታ ግን ለግብጽ መንግስት ብዙም የሚዋጥለት አልሆነም::

ግብጽ በመርህ ደረጃ ሳይቀር ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ፍትሀዊ የውሀ አጠቃቀም ዙሪያ የተቀመጡ ዓለም አቀፍ ህጎችን ሳይቀር ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኗ፤ መቼም ቢሆን በሕዳሴው ግድቡ ዙሪያ ገንቢ አተያይ ሊኖራት አይችልም። ለዚህም ነው በየጊዜው በምትፈጥረው አዳዲስ አጀንዳ ለማደናቀፍ የምትሞክረው:: ግራም ነፈሰ ቀኝ በኢትዮጵያ ላይ የምትሸርበው ሴራ በዚህ የሚያበቃ አይመስልም::

የግድቡ ግንባታ ከተጀመረበት ከአሥር ዓመታት በፊት ጀምሮ ግብጽ፣ ሱዳን እና ኢትዮጵያ በግድቡ አሞላል እና ኦፕሬሽን ከስምምነት ለመድረስ በርካታ ድርድሮችን አድርገዋል፤ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይም ስምምነት ላይ ቢደርሱም ስምምነቶቹን መሬት በማውረድ ሂደት ውስጥ ግን የግብጽ ዳተኝነት እንዳለ ነው።

ኢትዮጵያ የአባይን ውሀ ለብቻዬ ልጠቀም ሳትል፤ ሁሉን ተጠቃሚ በሚያደርግ መርህ ላይ በመመርኮዝ ታላቁን የህዳሴ ግድብ በመገንባት የውሃ ድርሻዋን በመጠቀም አገርና ህዝብን ተጠቃሚ ለማድረግ እየሰራች ነው:: ይህ ደግሞ በግብጽ በኩል ወንጀለኛ የሚያስብል እየሆነ ነው::

በርግጥ ግልጽነትን ለማስፈን ካልሆነ በስተቀር ዓለም አቀፍ ህግን ተከትሎ መስራት በራሱ የህጋዊነት ማረጋገጫና መሰረት ነው። ብዙ መጮህንና አድምጡኝ ማለትን የሚፈልግ አይደለም። ይህም ሆኖ ግን ኢትዮጵያ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እውነታውን በአግባቡ እንዲረዳና ከጎኗ እንዲሰለፍ ባለመሰልቸት በየጊዜው ድምጿን እያሰማች ትገኛለች::

አሁን ላይ የሕዳሴ ግድብ ሦስተኛ ዙር የውሃ ሙሌትም መጠናቀቁን ይፋ ከተደረገ በኋላ በሁለት ተርባይኖች አማካይነት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት ሥራ መጀመሩም የሚታወቅ ነው:: የግድቡ ግንባታም ከጥቂት ወራት በፊት 83 በመቶ መድረሱ ተገልጿል::

የሕዳሴው ግድብ ለኢትዮጵያውያን የኃይል ምንጭ ከመሆን ባለፈ አሁን ላለው ሆነ ለሚመጣው ትውልድ የይቻላል መንፈስ የዘር ፍሬ ሆኖ የሚያገለግል፤ የአገርና የህዝብን አንገት ቀና ማድረግ የሚያስችል የልብ ፈውስ የሚያመጣ ፕሮጀክት እንደሆነ ይታመናል። ይህም ኢትዮጵያውያን በሕዳሴ ግድብ ዙሪያ ወደኋላ የሚመልሳቸው አንዳች ነገር እንደማይኖር የማረጋገጫ ማሕተም ነው::

ለዚህም ነው ያለማንም ድጋፍ ያላቸውን ቋጥረው የታላቁን የሕዳሴ ግድብ ከፍ ባለ አንድነትና መተባባር ጀምረው አሁን ያለበት ደረጃ ያደረሱት፤ እስከ ፍጻሜውም ለመጓዝ በፅናት የተሰለፉት:: ትናንት በአድዋ ያሳዩትን ተምሳሌታዊ ገድል በግድቡ ለመድገም ቀን ከለሊት የሚተጉት:: ሰላም::

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# የሽግግር ፍትህ- ሁሉን አቀፍ የፍትህ ሚዛን

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

የሽግግር ፍትህ የቅርብ ጊዜ እሳቤ ሳይሆን ከዲሞክራሲ ውልደት ጋር አብሮ የተወለደ የፍትህና የስርዐት ትግበራ ነው።ከክርስቶስ ልደት ወዲያና ወዲህ በመሪና ተመሪ የአስተዳደር ስርዓት ውስጥ ከዲሞክራሲ ጋር መሳ ለመሳ የቆመ እንደነበር የኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲው ተመራማሪ ጆን ኤልስተርን ጥናት ጨምሮ ብዙ ማስረጃዎች ይጠቅሳሉ።

ሰብዐዊነትን አስቀድሞ ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደርን ያስከተለው የሽግግር ፍትህ ጽንሰ ሀሳብ ከጥንት ዘመን አንስቶ እስከ አሁኑ ድረስ በብዙ አገራት በማቀንቀን ላይ ይገኛል።የሽግግር ፍትህ በአጭር አማርኛ ለመግለጽ ከሰላምና ወደ እርቅ የሚወስዱ የፍትህ እሳቤ ማለት ይቻላል።

የሽግግር ፍትህ በተለይ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ወዲህ በሰብዓዊነት ላይ የደረሱ ጉስቁልናዎችን እንደ መነሻ በመውሰድ እንደ አንድ የሰላምና የዲሞክራሲ አማራጭ ሆኖ በስራ ላይ ውሏል።

ጨቋኝ አስተዳደራዊ መዋቅርን የሚሞግት፣ ለሰብዐዊነት የቆመና ለፍትህ የሚወግን የሰላም ሽግግር ሂደት ነው።የነበሩና ያሉ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግሮችን አይቶና ተረድቶ ለፍትህ የሚያቀርብ የተጠናና የተፈተሸ አሰራር ነው።

አገርና ህዝብ በተጎዱበት የፖለቲካ ስርዐት ላይ በዳዮችን ተጠያቂ እያደረገ ተበዳዮችን ፍትህ እንዲያገኙ የሚሰራ ነው።በጦርነትና በእርስ በርስ ግጭቶች፣ በዘርና በብሄር፣ በሌላም መሰል አለመግባባቶች ውስጥ የሚደርሱ ሰብዐዊ የመብት ጥሰቶች ተገቢውን ፍርድ እንዲያገኙ ለመብት ጥበቃ ቅድሚያ የሚሰጥ ነው።

ይሄን አስመልክቶ የህግ ባለሙያው አምሀ መኮንን እንዲህ ይላሉ ‹የሽግግር ፍትህ አንድ ስርዐት ወደሚታሰብ ሌላ አዲስ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ስርዐት የሚደረግ ሽግግር ነው።በዚህ ሽግግር ውስጥ የሚታዩ የከፉ የመብት ጥሰቶች እንዴት ይዳኙ የሚለው ምላሽ በሽግግር ፍትህ አለ።

ከሰሞኑ በመዲናችን አዲስ አበባም በሽግግር ፍትህ አማራጭ ሀሳቦች ዙሪያ የሚመክር አገር አቀፍ ጉባኤ ተካሂዷል።ውይይት የተካሄደው ከሲቪል ማህበራት፣ ከመገናኛ ብዙሃንና የዲሞክራሲ ተቋማት ጋር ሲሆን በጉባኤው ላይ ቀጣዩን የአገራችንን ዘላቂ ሰላም በተመለከተ ሐሳቦች ተንሸራሸረዋል።

መሰረታዊ የሽግግር ፍትህ በኢትዮጵያ እስከዛሬ ለተፈጸሙ ጉልህ በደሎች እውቅና መስጠት፣ ተጠያቂነትን ማስፈን እንደዚሁም ተጎጂዎችን መካስና ሌሎች ተመሳሳይ የሰብዐዊ መብት ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ እንደሚያስችል መተማመን ላይ ተደርሷል።

የፍትህ ሚኒስቴር በቅርቡ ይወጣል ባለው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ካስቀመጣቸው የማስፈፀሚያ ስልቶች ውስጥ ቀዳሚው ክስ ነው።ወንጀልን በመመርመርና በምርመራ ውጤቱ ላይ እንዳስፈላጊነቱ ክስ መመስረት ቀዳሚ ስልት ሆኖ ተቀምጧል።የክስ ስልት እንደ ቀዳሚ መስፈር ሆኖ መቀመጡ ተጠያቂነትን ለማስፈን መሆኑ ግልጽ ቢሆንም ከዚህ በተጓዳኝ ፍትህ በማምጣት ሂደት ላይም የጎላ ሚና ስላለው ጭምር ነው ።

ሌላኛው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ ስልት ሆኖ የተቀመጠው እውነትን ማፈላለግና የተገኘውን እውነት ይፋ ማድረግ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ እርቅ፣ ምህረትና፣ የገንዘብ ወይም ሌሎች ካሳዎችም በዚህ ማስፈጸሚያ ስልት ውስጥ ተጠቃለዋል።

ከላይ ያየናቸው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ ስልቶች ችግሮቻችንን ሽረው ዘላቂ መፍትሄ አማጭ እንደሚሆኑ እናምናለን።እንደአገር የተሸከምናቸውን የነውጥ እና የጦርነት ሀሳቦችን አርግበው የቀና መንገድ ያመላክቱናል ስንል ተስፋ እናደርጋለን።

የፍትህ ሚኒስቴር የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች በሚል ርዕስ ባወጣው ባለ 37 ገጽ ሰነድ ላይ ‹ከእርስ በርስ ጦርነት፣ ግጭትና ጭቆና በመውጣት በፖለቲካና በዲሞክራሲ ስርዐት ግንባታ ውጤታማ ሽግግር ለማድረግ በሞከሩ አገራት የሽግግር ፍትህ ሂደቶች ተግባራዊ ተደርገዋል› ብሏል።

በዚህ የሽግግር ፍትህ የተጠቀሙ እንደ ሩዋንዳ እና ደቡብ አፍሪካ የመሳሰሉ አገራትን መጥቀስ ይቻላል።ሩዋንዳ ውስጥ የተፈጠረውን የእርስ በርስ የጎሳ ግጭት ለማስቆምም ሆነ ተጠያቂነትን ለማስፈር የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እንደአንድ የመፍትሄ አካል ተወስዷል።

በግጭቱ ተጠያቂ የሆኑ አካላትን በመጠየቅና ለፍርድ በማቅረብ እንዲሁም ደግሞ የደረሱ የሰብዐዊ መብት ጥሰቶችን እንደየ አስፈላጊነታቸው ፍትህ እንዲያገኙ በማድረግ የሽግግር ፍትህ የበረታ አስተዋጽኦ ነበረው።በዚህ ብቻ አላቆመም የትላንቱን ዓይነት መሰል የዘርና የጎሳ ግጭቶች እንዳይነሱ በእርቅና በተግባቦት ላይ የተመሰረተ የአንድነት መንፈስም አቀዳጅቷቸዋል።

በደቡብ አፍሪካም ሆነ በሌሎች የዓለም አገራት ተመሳሳይ ነገር ነው የታየው።እንደ አገር የተፈጠሩባቸውን ፖለቲካዊና ማህበራዊ ተግዳሮቶቻቸውን በሽግግር ፍትህ በኩል ነው ያለፉት።ሁሉንም ትተን የደቡብ አፍሪካን ተሞክሮ ብናይ እንኳን አገራችን ብዙ መማር ትችላለች።በአፓርታይድ ስርዓት በነጮች የበላይነት ስር የነበረውንና በዘርና በብሄር የተከፋፈለውን አፍሪካዊ ማንነት መስመር ያስያዘው የሽግግር ፍትህ ነው።

ደቡብ አፍሪካውያን እንደ ዜጋ ያጡትንና የተነጠቁትን ዲሞክራሲዊ መብቶቻቸውን ያስመለሱት በሽግግር ፍትህ በኩል ነበር።የዚያን ዘመን የነጮች ጭቆናና የመብት ረገጣ በይቅርታና በቅጣት፣ በካሳና በእርቅ አልፈው ዛሬ ላይ አዲሷን ደቡብ አፍሪካ መፍጠር ችለዋል።

ይሄን መሰል አጋጣሚ አገራችን ራሷን እንድትፈትሽ ዕድል የሚሰጣት ነው።ከሩዋንዳና ከደቡብ አፍሪካ ልምድ በመውሰድ የነበሩና ያሉ ችግሮቻችንን በቁጥጥር ስር ለማድረግ ሩዋንዳውያን ምን ነበሩ፣ አሁንስ ምን ላይ ናቸው? ደቡብ አፍሪካውያን ከምን ተነስተው ነው ዛሬ ላይ የደረሱት? ስንል መጠየቅ መቻል አለብን።

አገራችን ከነዚህ አገራት የምትማረው ብዙ ነገር ይኖራል።ወቅቱ በብሄርና በፖለቲካ ሽኩቻ የምንናቆርበት ወቅት ነው።ግጭቶች ያላባሩበት፣ የሰብዐዊ መብት ጥሰት የሚታይበት አገር ውስጥ ነን።እኚህንና የመሳሰሉ ችግሮቻችን የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ይፈልጋሉ።

በጦርነትና በብሄር አስተሳሰብ የተለያዩ አጀንዳዎችን እያራመድን ባለንበት በዚህ ጊዜ በዳዮችን ለህግ በማቅረብና ተበዳይ ፍትህ እንዲያገኝ በማድረግ ረገድ የሽግግር ፍትህ ወሳኝ ሚና አለው።ያለፉት ታሪኮቻችን በዚህ መንገድ ካልሆነ በምንም ቢዳኙ አስፈላጊውን ውጤት ሊያመጡ አይችሉም።

የደቡብ አፍሪካ የሽግግር ፍትህ ከመንግስትም ሆነ ከየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ጣልቃ ገብነት የፀዳ ነበር።ይሄ መሆኑ ነው በተፈለገው መንገድ ውጤት እንዲያመጣ መንገድ የጠረገው።በእኛም አገር ተመሳሳይ ነገር መደረጉ ችግሮቻችንን በቶሎ ለማረቅ አቅም ይፈጥርልናል።

ነጻና ገለልተኛ በሆነ መንገድ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲን ተግባራዊ ያደረጉ አገራት ታሪክ እንደሚያሳየን ከሆነ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ መሬት ላይ ወርዶ ለውጥ እንዲያመጣ በአገራዊ ተግባቦት የተቃኘ፣ ለጋራ ለውጥ በጋራ የሚለፋ፣ ከፖለቲካ ነጻ የሆነ መዋቅር እንደሚያስፈልግ ነው።

**በጦርነት የዛሉ ብዙ ክንዶች አሉን፣ በውሸት የተዛነፉ፣ በፖለቲካ የተጣመሙ ከመዛነፍና ከመጣመም አልፈው ለጦርነትና ለእርስ በርስ ግጭቶች የዳረጉን ወቅታዊም ሆነ ነባር ችግሮች አሉብን።እኚህ ችግሮቻችን በሰብዓዊነት ላይ ያደረሱት ጉዳት ተመዝኖ መጪውን ጊዜ የተሻለ ከማድረግና ተመሳሳይ ጥፋት ካለመስራት አኳያ በሽግግር ፍትህ በኩል መዳኘት የተሻለ ብቻ ሳይሆን ተመራጭም ነው**

በቀጣይ በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ለውጥ ካመጡ አገራት ልምድና ተሞክሮ ወስደን ችግሮቻችንን እልባት መስጠት ትልቁ የቤት ስራችን ነው።መጪው ጊዜ በልምድና ተሞክሮ ታግዛ አገራችን ራሷን በእውነትና በፍትህ በተጠያቂነትም ራሷን የምታድስበት ይሆናል።

ብዙ አጀንዳዎች በሚራገቡበት በዚህ ጊዜ ፖለቲካዊም ሆኑ ማህበራዊ ነውሮቻችን የሚጠሩት እንዲህ ባለው ማንም በማይጎዳበት የፍትህ ሚዛን ነው።ይሄ ሚዛን አሁን ላለችው አገራችን በእጅጉ አስፈላጊ ነው።ጦርነት የፈጠሩ አስተሳሰቦቻችን፣ ብሄርና ዘረኝነትን የሚያቀነቅኑ ስርዓቶቻችን ተመዝነው የሚቀሉበት፣ ቀለው የሚቃኑበት የለውጥና የተሃድሶ እንቅስቃሴ ነው።

እንደአገር ልናስተካክላቸው የሚገቡ ብዙ ፖለቲካ ወለድ ትርክቶች አሉብን።ሁሉንም ትተን ባሳለፍናቸው አራት ዓመታት ውስጥ የታዩ ብሄር ተኮር ግጭቶችን ብናስብ እንኳን የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው እውን ማድረግ ወሳኝ ስለመሆኑ አብዝተው ይነግሩናል።

እርቅም ይሁን ምክክር፣ ካሳም ሆነ ተጠያቂነትን የሚሹ ጉዳዮቻችንን አንስተን እንደየአስፈላጊነታቸው ማረቅ መጪውን ጊዜ በአስተማማኝ ሁኔታ የምናይበት አንዱ መንገድ ነው።ጥፋተኞችን በጥፋታቸው እንዲጠየቁ የሚያደርግ ጠንካራ የፍትህ ስርዓት መገንባት አብሮ ሰላማዊ አገርን መገንባት ነው።

ጥፋተኞች በነጻነት የሚኖሩባት አገር ማብቃት አለባት።ፖለቲከኞች በብሄርና በዘር ተቧድነው ነውጥ የሚቀሰቅሱባት ኢትዮጵያ በሽግግር ፍትህ ፖሊሱ የተከናነበችውን ማቅ አውልቃ ፍትህ የሚሉትን የሰብዐዊነት አርማ መታጠቅ አለባት።ተጠያቂነት አገርን ወደፍትህ የሚመልስ መንገድ ነው።እየጠየቅንና እየተጠየቅን ካልሆነ በቀር እውነተኛ ተሃድሶ ማምጣት አይቻልም።

በጦርነት የዛሉ ብዙ ክንዶች አሉን፣ በውሸት የተዛነፉ፣ በፖለቲካ የተጣመሙ ከመዛነፍና ከመጣመም አልፈው ለጦርነትና ለእርስ በርስ ግጭቶች የዳረጉን ወቅታዊም ሆነ ነባር ችግሮች አሉብን።እኚህ ችግሮቻችን በሰብዓዊነት ላይ ያደረሱት ጉዳት ተመዝኖ መጪውን ጊዜ የተሻለ ከማድረግና ተመሳሳይ ጥፋት ካለመስራት አኳያ በሽግግር ፍትህ በኩል መዳኘት የተሻለ ብቻ ሳይሆን ተመራጭም ነው።

የሽግግር ፍትህ መነሻው አገርና ህዝብ ትውልድም ነው።መድረሻው ሰላምና ፍትህ ነው።በጦርነትና በአለመግባባት እየጠፋ ያለውን የህዝቦች አንድነትና ወንድማማችነት በምክንያታዊ እውነት መመለስ ነው።በክስም ሆነ በሌሎች ባህላዊ ዳኝነት በማህበረሰብ መካከል ተገኝቶ ወደቀደመ አንድነት መመለስ ነው።

የሽግግር ፍትህ ከነባሩ ፍትህ በተለየ መልኩ በፍርድና በካሳ፣ በቅጣትና በይቅርታ በእርቅም ከማህበረሰቡ ለማህበረሰቡ የወገነ የሰብዐዊነት መንፈስ ነው።የትግበራ ሂደቱም ሰውነትን ባስቀደመ ሁኔታ ሰላም ሊያመጡ የሚችሉ ማናቸውንም አማራጮች መጠቀም ነው።

የሽግግር ፍትህ ከጥላቻ ወደ አንድነት፣ ከጦርነት ወደሰላም፣ ከመብት ረገጣ ወደተጠያቂነት የምናደርገው የለውጥ ጉዞ ነው።ጉዞው ሰላም በማምጣትና ፍትህ በማስፈን ብቻ የሚጠናቀቅ አይደለም።ችግር ፈጣሪዎችን የሚቀጣ፣ ሰላም አምጪዎችን የሚያበረታታ ነው።የሽግግር ፍትህ ዋነኛ ባለቤት ህዝብ ነው።በዛሬና በትላንት ማዕከል ሆነው ሰላም የነሱን አስተሳሰቦች የምናርቅበት የአዲስ ታሪክ መጀመሪያ ነው።ከፊታችን ያሉ የለውጥና የዕድገት ተስፋዎቻችንን የምናይበት መነጽር ነው።

# ወቅታዊ

# «ስንዴ ላይ ተአምራዊ ለውጥ አምጥተናል፤ የቀረው እስኪትረፈረፍ ማምረት ነው»

**- የግብርና ሚንስትር ዶክተር ግርማ አመንቴ**

አስመረት ብስራት



የዛሬ የወቅታዊ እንግዳችን የግብርና ሚንስትር ዶክተር ግርማ አመንቴ ናቸው። ዶክተር ግርማ የቀድሞ ጎጃም ክፍለ አገር መተከል አካባቢ ነው ተወልደው ያደጉት።ትምህርታቸውንም እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ እዛው የተወለዱበት አካባቢ ከተማሩ በኋላ፤ በ1983 ዓ.ም የሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ ገቡ። ከዛ ለአራት ዓመት ተምረው የመጀመሪያ ዲግሪ በደን ሳይንስ ተቀብለዋል።ከዛም በኦሮሚያ ክልል ስራ ተቀጥረው ለሶስት ዓመት እንደሰሩ ለመማር ከፍተኛ ጉጉት ስለነበራቸው ለማስተርስ ወንዶ ገነት እና ስዊድን አገር በነበረ ሳንዱች ፕሮግራም ማስተርስ ዲግሪያቸውን በፕሮዳክሽን ፎረስትሪ ላይ ሰሩ፤ ከዛ የሶስተኛ ዲግሪ ከጀርመን አገር ከደን ሳይንስ ጋር የተገናኘ ትምህርት ተማሩ።

ዶክተር ግርማ በሞጆ ማገዶ ቴክኖሎጂ ፕሮጀክት፤ አስተባባሪ በምስራቅ ሸዋ ዞን የግብርና መምሪያ ኃላፊ፤ በኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ስር ይተዳደር የነበረ የአዳባ ዶዶላ የተቀናጀ የደን ማኔጅመንት ፕሮጀክት አስተባባሪ፤ በኦሮሚያ አርብቶ አደር ቆላማ አካባቢዎች ፕሮጀክት ኃላፊ፤ የሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት፤ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስትር፤ የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ቁጥጥር፤ የደን ኢንተርፕራይዝ ዳይሬክተር፤ የገጠር ልማት ዘርፍ ኃላፊ፤ የመንግስት ሀብት አስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት፤ የግብርና ሚንስትር በመሆን እስካሁን ድረስ በበሳል እውቀታቸው በግብርናው ዘርፍ አገራቸውን እያገለገሉ ይገኛሉ። ከእኝህ የካበተ የስራ ልምድ ባለቤት ከሆኑ የግብርና ባለሙያና የስራ ኃላፊ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እነሆ፤

**አዲስ ዘመን፤ በዚህ ሰፊ የስራ ልምዶት ግብርናው ላይ ምን አስተዋጽኦ አበረከቱ?**

**ዶክተር ግርማ፤** ከሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ እንደወጣሁ ሞጆ ነው ስራ የጀመርኩት። እዛ ማገዶ ቴክኖሎጂ ፕሮጀክት አስተባባሪ ሆኜ ለሶስት ዓመት እዛው ከሰራሁ በኋላ የማስተርስ ትምህርት ዕድል አግኝቼ ሄድኩ። ትምህርቴን ጨርሼ ስመጣ በዞን ደረጃ በምስራቅ ሸዋ ዞን የግብርና መምሪያ ላይ ለጥቂት ጊዜ ከሰራሁ በኋላ በኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ስር ይተዳደር የነበረ የአዳባ ዶዶላ የተቀናጀ የደን ማኔጅመንት ፕሮጀክት የሚባል በጀርመን ቴክኒካ ኮሚሽን የሚመራ ያንን ፕሮጀክት እንዳስተባብር በኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ተመርጬ ወደ ባሌ ዞን ዶዶላ ከተማ ሄድኩኝ። እዛ የተሰራው ትልቅ ነገር ለአገርም ተርፏል። የአገራችን ደን እንደሚታወቀው በዘበኛ ነው የሚጠበቀው፤ ዘበኛው እየጠበቀ ደኑ እየተቆረጠ ህዝቡም የኔ ነው ሳይል ቆይቷል። እዛ ስንሰራ እንዴት አድርገን ነው ህብረተሰቡን ያሳተፈ የደን እንክብካቤ ስልት የምንፈጥረው የሚል አሰራር የምንሞክርበት ግዜ ነበረ ፤ ሙከራው ተሳክቶ አርሶ አደሩ ተደራጅቶ የተወሰነ ደን ተከልሎ መጠቀም የሚችልበት ነገር ተነግሮት እንዴት መጠቀም እንዳለበት ተነግሮት፤ እየተንከባከበ እንዲጠቀም የማድረግ ስራ ነበር እና ድሮ ደን የግል እና የመንግስት ይባል ነበረ አሁን ሶስተኛ የህብረተሰብ የሚል ተጨምሮበት፤ በአሁኑ ሰዓት ህብረተሰቡን ያሳተፈ የደን ስርዓት እየተተገበረ ነው። ይህን ፕሮጀክት በማዘጋጀት ለእኔ በግሌ አንድ ዕድል ፈጥሮልኛል፤ የጀርመን ቴክኒካል ኮርፖሬሽን ነበር ድጋፍ የሚያደርግልን በነበረን ግንኙነት የፒኤችዲ ትምህርቴን እዛው አመቻችቼ ጀርመን አገር ለመማር ዕድል አግኝቻለሁ።

ፒኤችዲ ጨርሼ እንደተመለስኩ ኦሮሚያ ክልል ቢሮ ላይ ተመደብኩ። በ1997 ዓ/ም ከምርጫ በኋላ አዲስ አመራር ነበረ። ክልሉ ላይ በተለይ አባ ዱላ ገመዳ ወደ ፕሬዚደንትነት የመጡበት ስለነበረ በኦሮሚያ አርብቶ አደር ቆላማ አካባቢዎች አሁንም እየገጠመን ያለው የድርቅ ሁኔታ እንዴት አድርገን የምግብ ዋስትና እናረጋግጥ የሚለው ትልቅ ጥያቄ ነበረ።ያንን የሚያጠና ቴክኒካል ቡድን በሚዋቀርበት ወቅት አንዳንድ ሀሳቦችን በማቅረብ የቴክኒካል ኮሚቴውን እንዳስተባብር ተመረጥኩ።

በዚህም ወደ አርብቶ አደሩ ቆላማ ስፍራዎች አካባቢ በመሄድ ከማህበረሰቡ ጋር አብሮ ውሎ በማደር የአርብቶ አደሩን ችግር ለመፍታት በአካባቢው ስድስት ወራትን የፈጀ ጥናት በማጥናት የ2 ነጥብ 5 ቢሊየን ብር የፈጀ የኦሮሚያ ዲቨሎፕመንት ኮርደር በሚል ፕሮጀክት ተዘጋጀ።

ፕሮጀክቶቹ ከዚህ በፊት ታስበው የማያወቁ ናቸው። ለምሳሌ የከረዩ ማህበረሰብ ግመሎቹን ይዞ ውሀ ፍለጋ ይሰደድ ነበር። አጠገቡ አዋሽ እየፈሰሰ ለምን ይሰደደል በማለት አዋሽን ገድቦ ለከረዩ ህዝብ ለማቀበል የአዋሽና ፈንታሌ እሪጌሽን ፕሮጀክት ተሰራ።

ሌላው ጥናቱ ተግባራዊ ሆኖ አሁን ያለውን የቦረና ህዝብ ችግር ባይፈታም የቦረናን ህዝብ ችግር የተጠናው ከዓመታት በፊት ነው። የቦረና ህዝብ ጥያቄ ውሃ ነበር። ውሃ ከየት ይገኛል ተብሎ ሲታሰብ፤ ቦረና ላይ ወንዝ የለም፤ ዝናብ አጠር አካባቢ ነው፤ የከርሰ ምድር ውሃ ብዙ ጊዜ ይቆፈራል ግን ተገኝቶ አያውቅም። ስለዚህ በክልሉ ያለውን የከርሰ ምድር ውሃ ሲጠና ውሃው ከኬኒያ ድንበር አስር ኪሎ ሜትር ላይ ሰውም አይኖርም። ከብትም የማይሄድበት ቦታ ላይ ተገኘ። ይህን ውሃ ቆፍረን አጓጉዘን ተራራ ላይ ካወጣነው በኋላ በምድር ስበት ሁሉንም የቦረና ክፍል ማዳረስ ይቻላል የሚል እቅድ ታቅዶ ነበር። ይህ ጥናት ብዙ ቦታዎቹ በማቅረቤ የተነሳ በኦሮሚያ ውሃ ዲዛይንን ቁጥጥር ኢንተርፕራይዝ ምክትል ስራ አስኪያጅ በመሆን ለማገልገል በቃሁ።

የመሬት ኢንተርፕራይዝና ግብርና ዘርፍ ነበር ለኔ የተሰጠው። መሬት ለምን መዋል አለበት? በየትኛው መሬት ላይ ለተሻለ አገልግሎት ሲውል አይታይም። የጤፍን መሬት ለመጋዘን እናውላለን የእርሻን መሬት ለከተማ ታደርጊያለሽ የደንን መሬት በፍፁም ሌላ አገልግሎት መዋል የሌለበትን ለሌላ እናውላለን። ስለዚህ እንዴት አድርገን ነው የበለጠ ውጤታማ የምናደርገው፤ አንድ መሬት ለጤፍ፤ ለቡና ለበቆሎ ብቻ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እንዴት አድርገን ነው መሬቱን ለተገቢው አገልገሎት የምናውለው በማለት የመሬት አጠቃቀም ጥናትን ኦሮሚያ ውስጥ ያስጀመርኩት እኔ ነኝ።

በዛን ጊዜ አንድም የተጠና ጥናት አልነበረም። አሁን ኦሮሚያ መቶ በመቶ የመሬት አጠቃቀም ጥናት ተጠንቶ እቅድ ወጥቶለት በአዋጅ ተደግፎ ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓዋል።

እዛው ኢንተርፕራይዝ እያለሁ ሌላ ኢትዮጵያ ካላት ደን ውስጥ አብዛኛው ያለው ኦሮሚያ ውስጥ ነው። ደን ለአየር ንብረት ለውጥ፤ ለአፈርና ለውሃ ጥበቃ ብቻ ሳይሆን እኔ የተማርኩባቸው ስዊዲንና ጀርመን ከደን ንብረት በጣም ከፍተኛ ምርት ነው የሚያገኙት። በዚህም ለምን ደኑን ለኢኮኖሚያዊ ጥቅም አናውለውም በሚል ጥናቱ ተጠንቶ የኦሮሚያ ደንና ዱር እንሰሳት ድርጅት እንዲቋቋም የመጀመሪያውን ጥናት ከመሩት ሰዎች መካከል አንዱ ነኝ። የማስጀመሪያ ስራዎች ተጠናቀው ኢንተርፕራይዙ ሲቋቋም ዋና ዳይሬክተር በመሆን የኦሮሚያ ዱር እንስሳት ድርጅትን በመምራት ለአምስት ዓመታት አገልግያለሁ።

ደን እዚህ አገር ገንዘብ ያመጣል ተብሎ ተጠብቆ አያወቅም። መብራት ኃይል የተቀቀለ ባህር ዛፍን ለኤሌክትሪክ ምሰሶነት ከደቡብ አፍሪካ ያመጣ ነበር፤ ቡና ሸጠን ባህር ዛፍ እንገዛ ነበር። ኢኮሎጂስቶች ደግሞ ባህር ዛፍ አገሪቱን ወሯል በሙሉ ባህር ዛፍ ነው ያለው እያሉ በሚያማርሩበት ወቅት ነበር።

በወቅቱ የመብራት ኃይል የበላይ ኃላፊ ከነበሩት ጋር በመነጋገር ባህር ዛፍን ከአገር ውስጥ ለማቅረብ የ52 ሚለየን ብር ስምምነት ከመብራት ኃይል ጋር ተፈራርመን ስራ የጀመርኩት። አሁን የኦሮሚያ ደን ኢንተርፕራይዝ ማለት በዓመት ትልቅ ገቢ የሚያስገባ ተቋም ሆኖ ነው ያለው።

ከዛ የመጀመሪያ ዲግሪዬን በተማርኩበት ሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ እንድመራ ጥሪ ተደረገልኝ። እኔ እንኳን ዩኒቨሪሲቲ ሄዶ የመምራት ፍላጎት ባይኖረኝም በወቅቱ አስተዳደር አካባቢ የነበረውን አለመግባባት ለመፍታት በሚል ሄጄ ለሶስት ዓመታት አገልገያለሁ። ለኔ የተማርኩበትን ዩኒቨርሲቲ ማስተዳደሬ በጣም አስደሳች ጊዜ እንዳሳልፍ አድርጎኛል።

ከዛ በኋላ ለአንድ ዓመት የጥናት ፈቃድ በመውሰድ ጀርመን አገር ቆየሁ። ከዛ ስመለስ አዲስ ካቢኔ በቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ እየተቋቋመ ነበር። በእሳቸው ካቢኔ ውስጥ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስትር ሆኜ እንዳገለግል ጥሪ ቀረበልኝ። በዛ ወደ ሁለት ዓመታት ከሰራሁ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ሲመጡ ክልል ላይ እንደገና ያንተ ድጋፍ ይፈለጋል ተብሎ ወደ ኦሮሚያ ተመልሼ በገጠር ልማትና ግብርና ዘርፍ በምክትል ፕሬዚዳንት ማእረግ ለሶስት ዓመታት ሰርቻለሁ።

ይሄኛው ጊዜ በህይወቴ እንደ ትልቀ ቁምነገር የሰራሁበት ጊዜ ነው ብዬ አስባለሁ። በተለይ የአገራችንን ግብርና ከኋላ ቀር ወደ ዘመናዊ መዋቅራዊ ሽግግር የምናደርገው የሚል ሀሳብን አሰብኩ። ድሮም በኢህአዴግ ጊዜ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ሽግግር የሚባል አካሄድ ነበር፤ ግን አልተሳካም። ምክንያቱም ግብርናው ራሱ አልተሻገረም ነበር፤ ግብርናው ሳይሻገር ወደ ኢንዱስትሪ መሻገር አይቻልም። የተለያዩ የዘርፉን ምሁራን በማሳተፍ የኦሮሚያ የግብርና ሽግግር ሮድ ማፕ በማዘጋጀት ይሄንን ስራ በበላይነት መርቻለሁ።

በዚህ ውስጥ ነው እንግዲህ ሮድ ማፑን ሰርተን ከጨረስን በኋላ ኦሮሚያ ውስጥ ወደ አስራ አምስት የግብርና ኢኒሼቲቮችን ቀርፀን የስንዴ፤ የአቮካዶ፤ የአትክልትና ፍራፍሬ፤ የቡና፤ የማር ስራዎች የተተገበሩበት፤ ባለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት ኦሮሚያ የገጠር ልማት ዘርፍ ላይ የመጡት ውጤቶች ላይ የራሴን የጎላ አስተዋፅኦ አበርክቻለሁ። ከዛም የተነሳ ይመስለኛል አሁን ያለሁበትን የግብርና ሚኒስትርነትን አመራር ቦታ የተገኘሁት።

**አዲስ ዘመን፤ በግብርናው ዘርፍ በርካታ ስራዎችን ሰርተዋልና በስራዎት ላይ የገጠሞት ተግዳሮት ካለ ቢገልፁልን?**

**ዶክተር ግርማ፤** በህይወት ዘመኔ ስራ ላይ ያሳለፈኩት በፕሮፌሽናልና ቴክኒካል ስራዎች ላይ ነው። ነገር ግን በአመራር በሰራሁባቸው ቦታዎች ላይ ብዙ ሰዎች የሚያቁኝ ስራዬን ለማሸነፍ በርካታ ጥረቶችን አደርጋለሁ፤ ለስራዬ ሙሉ ለሙሉ ራሴን ሰጥቼ ነው የምሰራው፤ ራስን ለስራ በመስጠት ስራ ለማሸነፍ ሲሰራና ሌሎችን በማስተባበር መስራትን እወዳለሁ። እስካሁን በሰራሁባቸው መስሪያ ቤቶች በምስጋናና በስኬት አገልገያለሁ።

በሁሉም የስራ ሂደት ውስጥ ተግዳሮቶች አይጠፉም፤ ግን እነዛን ተግዳሮቶች አንድ ላይ በማስተባበር የመፍታት በርጋታ ነገሮችን የማየት አመለካከት አለኝና በእውነት የትኛውም የፖለቲካዊ ይሁን አስተዳደራዊ ይሁን በቋንቋ ተግባብቶ የመስራት አካሄድ አለኝ።

በአብዛኛው ምሁራኑ በሚያውቀው ልክ ሌሎች እንዲረዱት የመፈለግ ሁኔታ ስላላቸው በቢሮክራሲዎች ውስጥ ተቋቁሞ የማለፉ ነገር አይሆንላቸውም። እኔ ግን ከነገሮች ጋር ራሴን በማላመድ ቶሎ ተግባብቶ የመስራት ባህሪ ስላለኝ ብዙም አልተቸገርኩም።

እስካሁን በመጣሁባቸው ሂደቶች ካየሁት ግብርና ዘርፍ ማለት የአገሪቱን ሰማኒያ ከመቶ በላይ ህዝብ በአንድም በሌላ መልኩ ተፅእኖ የሚፈጠር ዘርፍ ነው። በጣም ብዙ ባለድርሻዎች ናቸው ያሉት። ብዙ አጋር ድርጅቶች፤ ብዙ ተጠሪ ተቋማት አሉት፤ ከብዙ ሚኒስትሮቸ ጋር ያገናኛል፤ ከብዙ የግሉ ዘርፍ ጋር ያገናኛል፤ ብቻ የሚሰራ ስራ ሳይሆን በጋራ በማስተባበርና በማቀናጀት የሚሰራ ስራ ነው። አሁን ወደዚህ ኃላፊነት ከመጣሁባቸው ሁለት ወራት ጀምሮ እያደረኩ ያለሁት ከባለድርሻዎች ጋር ግንኙነትን የመፍጠር የማስተባበርና የማቀናጀት ስራ ነው።

ስራውን ታች ሆኜም እሰራው ስለነበር ወደዚህ ዘርፍ ስመጣ አዲስ አልሆነብኝም። ነገር ግን እዚህ ጋ ያለው ባለድርሻ ብዙ ስለሆነ በርካታ ስራ እንደሚጠበቅብኝ አይቻለሁ። ዘርፉ የአገር ቁልፍ የሆነ፤ ለህዝብም ለአገርም ወሳኝ የሆነ በጣም ትልቅ ኃላፊነትና ትልቅ ክብር በመሆኑ ይህንን ኃላፊነት በውጤት ለመወጣት ቆርጫለሁ።

አሁን በጀመርነው አካሄድ ከታች ካለው የአርሶ

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

አደር ማህበረሰብ ጀምረን በየደረጃው ያለው አመራሩ ድረስ የግብርና ቤተሰብን የማስተባበርና የማቀናጀት ስራ ከሰራን በአረንጓዴ ልማት፤ በስንዴ ኢኒሼቲቭ፤ በሌማት ቱሩፋት ላይ የምግብ ሉአላውነትን ማስከበር ላይ ስራ ይዘናል። ስንዴ ለምን መብላት የለብንም የሚል ትልቅ አገራዊ ኃላፊነት ይዘናል። ይሄንን በእኔ የሚኒስትርነት ዘመን አሳካዋለሁ ብዬ አስባለሁ።

**አዲስ ዘመን፤ የቦረናን ህዝብ ችግር የሚቀርፍ ፕሮጀክት አጥንተን ነበር ብለዋል የፕሮጀክቱ መጨረሻ ምን ሆነ?**

**ዶክተር ግርማ፤** እኔ በተፈጥሮዬ አዳዲስ ሀሳቦችን ማሰብ ያንንም ለፖሊሲ ቀራጮች ማቅረብ መገለጫ ነው። ካቀረብኳቸው አዳዲስ ሀሳቦች ውስጥ ብዙዎች ተተግብረዋል። ለምሳሌ የመሬት አጠቃቀም እቅድ አልነበረም። ለመጀመሪያ ጊዜ ኦሮሚያ ላይ ያስጀመርኩት እኔ ነኝ። አሁን ሙሉ ለሙሉ ኦሮሚያ ላይ ተግባራዊ ሆነዋል። የኦሮሚያ ደን ኢንተርፕራይዝ ለመጀመሪያ ጊዜ አገር ውስጥ የተቋቋመው በኛ ጊዜ ነው አሁን ሌሎች ክልሎች እየወሰዱት ይገኛሉ።

በቆላማና አርብቶ አደር አካባቢ ብዙ የመፍትሄ ሀሳብ አቅርበናል፤ የፈንታሌ ፕሮጀክት ተሳክተዋል፤ ቲቢላ ፕሮጀክት ተሳክተዋል ብዙ ፕሮጀክቶች ተሰርተዋል። ቦረናም ተጀምሮ ነበር። ተጀምሮ አመራር ሲቀየር ከአንድ ሁኔታ ወደ ሌላ ሲኬድ ሁኔታዎች ይቀያየራሉ። የዛን ጊዜ የተጀመረው ፕሮጀክት ተጠናቆ ቢሆን ኖሮ ዛሬ የምንሰማው የረሃብና ሰቆቃ አይታይም ነበር።

አሁንም ቢሆን የቦረናን ህዝብ የውሀ ችግር በዘላቂነት ለመፍታት መፍትሄው ውሃ ማቅረብ ነው። ውሃን ለመጠጥ ብቻ ሳይሆን፤ መኖ ለማልማት መስኖ ለመስራት ማቅረብ አለበት። ባለፈው ዓመት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንድ ቢለየን ብር መድበው ወደ መቶ ኪሎ ሜትር መስመር በዛ እየተሰራ ነው። ተጨማሪ ወደ አምስት ሚሊየን ብር የሚፈልግ ፕሮጀክት ነው። አልቆ የቦረናን ህዝብ እስከመጨረሻው እፎይ ያስብላል ብዬ አስባሁ።

**አዲስ ዘመን፤ አሁንም ሆነ ወደፊት ለቦረና ህዝብ ምን ቢሰራ ነው ከሚታየው የከፋ የድርቅ አደጋ መውጣት የሚችለው?**

**ዶክተር ግርማ፤** የአየር ንብረት ለውጥን ድርቅን ማስወገድ አይቻልም። ዋናው ቸግር እኛ አለመዘጋጀታችን ነው። በኔ ሀሳብ ቦረና ብቻ ሳይሆን በመላው አገሪቱ የሚገኙ ቆላማ ቦታዎች የአርብቶ አደሩ ጥያቄ ውሃ ነው። በጥናቱ ወቅት አርብቶ አደሩ እንደሚለው "ትምህርት ቤት ይሰራል፤ ጤና ተቋም ይሰራል፤ እኛ ግን ውሃ ፍለጋ ትተነው እንሄዳለን ስለዚህ ውሃ አቅርቡልንና እንቆይ" ነው።

ችግሮቹ እየታወቁ ከተጠኑ ዓመታትን እያስቆጠሩ በጀት በጅቶ የመፍትሄ ስራ ላይ መረባረብ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው። በርካታ የመፍትሄ ሀሳቦች አሉ ዋናው ውሃ የሚገኝበትን ሁኔታ መማቻቸት ነው።

**አዲስ ዘመን፤ ደን ላይ ሰፋ ያለ እውቀት አሎት። በአገራችን የደን ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ደን ላይ ምን ቢሰራ የሚል ምክረ ሀሳብ ያካፍሉናል?**

**ዶክተር ግርማ፤** አሁን ያለው የደን ምርምር የሚያሳየው ወደ ተፈጥሮ ቅርብ ነው። ይህ ማለት ኮሶ ያለበት ቦታ ኮሶ መትከል፤ ዝግባን የሚበቅልበት ቦታ ካለ ዝግባ መትከል ምንም ምርምር ሳያስፈልገው ማለት ነው። ዛፎች ባጠቃላይ የተወሰነላቸው ቦታ ላይ ውጤታማ የሚሆኑበትን መትከል አለበት። በዚህም ከደን የሚፈለገውን ያህል ጥቅም ማግኘት አለበት።

አረንጓዴ ልማት ከፍተኛ ኃላፊነት ተወስዶ የሚሰራበት ጊዜ ላይ ነን ይህን እንደተማረ ሰው ቦታ በመምረጥ ስኬታማ የሆነ ስራ መስራት ይቻላል።

አገሪቱ ያላትን አገር በቀል የተፈጥሮ ደንን መጠበቅ የግድ ነው። ደኖችን ስንተክል ከአየር ንብረት ጥበቃ በላይ ከውጭ የሚመጡትን ለማስቀረት የሚያስችሉ ስራዎች መሰራት አለበት። ደን ሲተከል ለኢኮኖሚ አላማ፤ ለአካባቢ ጥበቃ እንዲሆን አድርጎ መተከል አለበት። ሁሉም ለአላማው በሚመች መልኩ መተከል አለበት፤ እሱ ጋር ይቀረናል።እነዚህ የሚተከሉ ደኖች የኢንዱስትሪ ጠቀሜታ እንዲኖራቸው የማድረግና የማስተሳሰር ስራ ላይ ይቀረናል ይሄንን መስራት አለብን።አንድ እኔም ያስጀመርኩትና የምኮራበት ስራ የደኖች የካርበን ፑል ናቸውና ዓለም ላይ አሁን ካለው የአየር ንብረት ለውጥ አንፃር ካርቦንዳይ ኦክሳይድ ከአየር ይወስዳሉ፤ ደኖች እንደ አንድ ፋብሪካ ናቸው።ካርቦንዳይ ኦክሳይድ ይመጣሉ፤ ኦክስጂን ይለቁልናል።ይህንን ካልኩሌት ማድረግ ይቻላል፤ አንድ ጋርደን ምን ያህል ይመጣል የሚለውን።ይህንን በባሌ ተራራዎች ላይ ነበር የጀመርነው እንደ ፓይለት ኦሮሚያ ውስጥ ባለፈው ዓመት አርሶ አደሮች ደን በመጠበቃቸው ወደ 300 እና 400 ሚሊዮን ክፍያ ተቀብለዋል።አብዞርቭ ያደረጉት ካርቦን ተለክቶ የዓለም ባንክ 40 ሚሊዮን ዶላር የካርበን ግዢ ከኦሮሚያ ለመፈፀም ቃል ተገብቷል።ስለዚህ የተፈጥሮ ደኖች የካርበን ጥቅም አላቸው የኢኮቱሪዝም ጥቅም አላቸው፤ የብዝሀ-ህይወት ጥቅም አላቸው።ሰው ሰራሹ ደን ለኢንዱስትሪ ለወረቀት ለፓልም እና ለብዙ ነገር መጠቀም አለብን።ኢትዮጵያ ውስጥ ደንን በኮሜርሻል ከመጠቀም አንፃር የደን ውጤት አዘጋጅታ ጥቅም ከማግኘት አንጻር አልተሰራም፤ ገና ብዙ መስራት ይጠበቅብናል።

**አዲስ ዘመን፤ የደን ጉዳይ ከተነሳ በተለይም የአገር በቀል የተፈጥሮ ሀብትን ጠብቆ በማቆየት ብዝሃ ህይወት ኢንስቲትዩት እየሰራ ይገኛል፤ በአብዛኛው ግን በቂ ድጋፍ እንደሌለው ይናገራሉ፤ ግብርና ሚኒስቴር ተቋሙን በምን መልኩ ይደግፋል?**

**ዶክተር ግርማ፤** እኔ የማምነው አብዛኛው የምርምር ተቋሞቻችን ብዝሃ ሕይወትን ጨምሮ ቴክኒካል ምርምሮች ተሰርተው ሊሆን ይችላል፤ ያ የተሰራው ምርምር ተደርጎ አገር ብትጠቀምበት በበቂ ሁኔታ አስተዋውቀናል፤ ከዚያ ውጪ የጋን ውስጥ መብራት ነው።አሪፍ ቴክኖሎጂ በእጅሽ ላይ ሊኖር ይችላል፤ ምንድነው ሊያመጣው የሚችለው ጥቅም የሚለውን አስተዋውቀን ከዚያ በኋላ ነው እንዱስትሪዎች ሊወስዱ የሚችሉት። አንዳንዱ እንዱስትሪ ወስዶ ኮሜርሻላይዝ ላያደርገው ይችላል።ለምሳሌ አንዳንዱ ከብዝሃ ህይወት ጋር ያሉት ዝርያዎች ውስጥ ኢንዱስትሪ የሚወስዳቸው በጣም መዓዛማ የሆኑ፤ ዘይት የሚወጣቸው በጣም ብዙ አውቃለሁ፤ መጀመሪያ ላይ አስተዋውቀናቸዋል ወይ ነው እንጂ እኔ በቃ ምርምር ሰርቼ የሆነ ጆርናል ላይ ስላሳተምኩ ውጤታማ ሆንኩ ማለት አይደለም።እንግዲህ አንድ ተጠሪ ተቋም ለኛ ብዙ መስራት ከሚገባቸው ይህች አገር ሸጣ ካልተጠቀመቻቸው አንዱ የብዝሃ ሀብቷን ኮሜርሻላይዝ ማድረግ ላይ ነው የሚቀረን።የእኛ ብዝሃ ህይወት ኮሜርሻላይዝ አልተደረገም።ስለዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ይሄን ያህል የብዝሀ ህይወት ዝርያዎች አሉ ቢባል ዳቦ ይሆናል እንዴ? አለ ማለትኮ የሆነ ጥቅም አለው ማለት ነው እሱን መሸጥ አለብን።ከዚህ አንፃር ብዙ አልሰራንም ብዙ መስራት አለብን የሚል ሃሳብ ነው ያለኝ።

**አዲስ ዘመን፤ ስንዴ በስፋት እየተመረተ ነው፤ የአገር ውስጥ ገበያ ላይ ደግሞ እጥረት አለ ይባላል። ስለዚህ ጉዳይ ቢያብራሩልን?**

**ዶክተር ግርማ፤** ኢትዮጵያ የስንዴን ዘር ለዓለም አስተዋፅዖ ያደረገች አገር ናት ተብላ ነው የምትታሰበው።የብዝሃ ሕይወት ሜጋ ዳይቨርሲቲ ማዕከላትን አነጋግረሽ ከሆነ የሚነግሩሽ ጃርገኖች አሉ፤ ኢትዮጵያ የባዮ ዳይቨርሲቲ ሆትስፖት ነች፤ የብዝሃ ሕይወት ማዕከል ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ኢትዮጵያ የስንዴ የመጀመሪያ በሽታን ከሚቋቋሙ የስንዴ አይነቶች ባለቤት ነች።አብዛኛው ስንዴ ወደ ሌላ ቦታ የሄደው ከዚህ ነው የሚባለው፤ ስለዚህ ስንዴ ለኛ አዲስ አይደለም።ስንዴን እኛ አስገብተን መብላት የጀመርነው ቅርብ ጊዜ ነው፤ ድሮ አባቶቻችን ስንዴን ክረምት ላይ ይመረታል ይበላሉ፤ ስለዚህ ስንዴ ማምረት ለኢትዮጵያ አዲስ አይደለም።እውነት ለመናገር ግን ስንዴን ካለን የአየር ሁኔታ አንፃር ስንዴን አሁን ከጀመርነው ቀድመን በስንዴ ራሳችንን ችለን ኤክስፖርት ማድረግ የነበረብን አገር ነን።ስለዚህ ስንዴ እዚህ አገር ውስጥ አዲስ ምርት አይደለም የነበረ ነው የጄኔቲክ ሀብቱ ባለቤት ነን።

አሁን ያለው ነገር ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ የወሰዱት ትክክለኛ ውሳኔ ነው ብዬ የማስበው ስንዴን ገዝተን መብላት የለብንም፤ ስንዴን እየተረዳን መብላት የለብንም የሚለው ነው።ይህ በጣም ትክክለኛ ውሳኔ ነው።ስሜታዊ ውሳኔ አይደለም አቅሙ አለን፤ አቅሙ ስላለን በ2 እና በ3 መንገድ ነው ለመስራት ያሰብነው፤ አንዱ ድሮም ስንዴ በክረምት ባሌ ላይ ይዘራል፣ ደጋማ ቦታ ላይ ይዘራል። ይህንን ደግፈን ብዙ ቴክኖሎጂ ሰጥተን እንስራ ነው።አዲስ ነገር የመጣው በበጋ ስንዴ እናምርት ነው።ግብፅ በዚያ በረሃ በመስኖ ከእኛ የተሻለ የስንዴ ምርት ታመርታለች።ውሃ ከተገኘ በበጋ ይመረታል። ይህ አዲስ ቴክኖሎጂ አይደለም።እኛ ነን የዘገየነው እንጂ ይህ ዓለም ላይ ያለ ነው።እንዲያውም ብዙ ተመራማሪዎች እስካሁን ምንድነው አይናችንን የያዘው ይላሉ።ለምሳሌ ባሌ ወይም አርሲ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ ስንዴ 90 ቀን የሚወስድ ከሆነ በበጋ ቆላማ ቦታዎች ላይ በ60 እና 70 ነው የሚደርሰው፤ ምክንያቱም ሙቀት አለ ቶሎ ይደርሳል።የበሽታ ነገር ሁሉ ይቀንሳል ምክንያቱን ውሃ ተመጥኖ ነው የሚሰጠው።ይህንን እንጨምርበት ተባለ። ስለዚህ ይሄ ፖለቲካል ቁርጠኝነቱ መጥቶ አሁን እንስራ ተባለ እንጂ ትላንት ነው መስራት የነበረብን።ይህ ፖለቲካ አይደለም ፕሮፌሽናል ነው።ሌላም አገር ተሰርቷል።አፈርን ተንከባክቦ ስንዴ ማምረት ኮቲቻ አፈር እየተባ የመጡ ነገሮች አሉ።ስለዚህ አሁን ጉዳዩ ስንዴ ማምረት በመጀመሪያ እኛ ያሰብነው አምርተን ራሳችንን መቻል ነው እሱን አሳክተናል።አሁን ፖለቲካ የሆነው እኛ በስንዴ ራሳችንን መቻላችን አይደለም፤ ስንዴን ኤክስፖርት እናደርጋለን ስንል የመጣ ጉዳይ ነው።ምክንያቱም ይህች አገር ስንዴ ስትረዳ ስንዴ ስትቀለብ ነው የኖረችው።ስለዚህ ይህ ለበርካታ ስንዴን ኢንፖርት አድርገው ለሚጠቀሙ በርካታ የአፍሪካ አገራት ጭምር መሰረታዊ ለውጥ ነው።ለዚህ ነው አትችሉም ይህንን ለማድረግ ገና ናችሁ የሚለው ነገር በተለያየ ግልፅም ግልፅም ባልሆነ መንገድ የሚመጣው።

እኔ ሲጀመር ጀምሮ አብሬ ነበርኩኝ። መልካ ወረርና አፋር ላይ ሲሞከር ምርምር ማዕከል ውስጥ ነበር የነበረው። ቀጥሎ ሰባት ሺ ሄክታር ላይ፤ ቀጥሎ ሶስት መቶ ሺ፤ ቀጥሎ ስድስት መቶ ሺ ሄክታር ላይ አሁን ደግሞ አንድ ነጥብ ሶስት ሚለየን ደርሰናል። በበጋ ብቻ 52 ሚለየን ኩንታል ሊመረት ችሏል። በፊት ይሄን ያህል መሬት በበጋ አይደለም ሶስት ኩንታል አምርተን አናወቅም ነበር።

ስንዴ ዘንድሮ ከገበያ ወጣ የለም ቢባል እኔን አያስደንቀኝም። ስንዴ ላይ ተአምራዊ ለውጥ አምጥተናል። የቀረው እስኪትረፈረፍ ማምረት ነው። በሚቀጥለው ዓመት አሁን ባመረትነው ልክ 2 ሚሊየን ሄክታር ብናመርት አለቀ። ይሄንን ደግሞ ከዚህ ቀደም አይተናል። የአሰላ ብቅል ፋብሪካ ለቢራ ገብስ አገር ቤት ያስገባል። ባለፈው ሶስት ዓመታት በተሰራው ስራ የቢራ ገብስ ብቅልን ከአገር ውስጥ ፍጆታ ተርፎ ለውጭ ተልኳል። አሁን ባለው ሰው ሰራሽ የገበያ ጉዳዮችን አፍ ለማዘጋት በተጨማሪ ማምረትን ይጠይቃል።

**አዲስ ዘመን፤ ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን።**

**ዶክተር ግርማ፤** እኔም አመሰግናለሁ።



**አሁን ያለውን የቦረና ህዝብ ችግር ባይፈታም የቦረናን ህዝብ ችግር የተጠናው ከዓመታት በፊት ነው። የቦረና ህዝብ ጥያቄ ውሃ ነበር። ውሃ ከየት ይገኛል ተብሎ ሲታሰብ፣ ቦረና ላይ ወንዝ የለም፤ ዝናብ አጠር አካባቢ ነው፤ የከርሰ ምድር ውሃ ብዙ ጊዜ ይቆፈራል ግን ተገኝቶ አያውቅም**

# የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ጉዞ

**አንተነህ ቸሬ**

ከዚህ ቀደም በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ስር የነበሩትን የምዕራብ ኦሞ፣ የቤንች ሸኮ፣ የካፋ፣ የዳውሮና የሸካ ዞኖች እና የኮንታ ልዩ ወረዳን (ልዩ ወረዳው አሁን በዞን ደረጃ ተደራጅቷል) በአንድነት በመያዝ በኅዳር ወር 2014 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲዊ ሪፐብሊክ 11ኛው ክልላዊ መንግሥት ሆኖ የተዋቀረው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል፤ ለኢንቨስትመንት የሚሆን ከፍተኛ አቅም ያለው በተፈጥሮ ሀብት የታደለ አካባቢ ነው፡፡ በተለይም ክልሉ ያለው የቡና፣ የሻይ ቅጠል፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የማዕድናት ሀብት ሀገርን የሚያኮራ፣ ባለሀብቶችን በኢንቨስትመንት ለመሰማራት የሚያነሳሳ እና የሕዝብን የልማት ጥያቄ ለመመለስ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥር መልካም ፀጋ ነው፡፡

የክልሉ ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ኤጀንሲ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ ክልሉ ወርቅን ጨምሮ የተለያዩ ማዕድናት ባለቤት ነው፡፡ ከወርቅ ማዕድን በተጨማሪ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውል የድንጋይ ከሰል በክልሉ በዳውሮ እና በኮንታ አካባቢዎች በስፋት ይገኛል። ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆን የብረትና የድንጋይ ከሰል ማዕድናትም ሌሎች በክልሉ የሚገኙ ሀብቶች ናቸው፡፡ በአስር ዓመቱ ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል የማዕድን ዘርፍ አንዱ በመሆኑ ዘርፉ በሀገራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ጉልህ ድርሻ እንዲኖረው በክልሉ ያለውን እምቅ ሀብት ጥቅም ላይ ለማዋል ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

የማዕድን ሀብቶችን ለይቶና አደራጅቶ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ የክልሉ ቀጣይ የቤት ሥራ እንደሆነ ግንዛቤ ተይዞ ከወዲሁ እየተሰራ እንደሆነም የኤጀንሲው መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተለይም ለውጭ ገበያ ቀርቦ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ረገድ ትልቅ ድርሻ ባለው በወርቅ ማዕድን ልማት ላይ በስፋት እንዲሰራና በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከውጭ በግዥ ጥቅም ላይ እየዋለ ያለውን የድንጋይ ከሰል በአገር ውስጥ መተካት እንዲቻል ትኩረት ተሰጥቷል፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት የሀገር ኢኮኖሚን በብርቱ የሚደግፉ ምርቶች መገኛ ነው፡፡ ከፍተኛ የቡናና የማዕድን ሀብቶችን የያዘው ይህ ክልል፤ ሀብቱ ከክልሉ አልፎ ለሀገርም የሚተርፍ ፀጋ ነው፡፡ ክልሉ አስደናቂ የሆነ መልከ ዓምድራዊ አቀማመጥ፣ ልምላሜና የተፈጥሮ ሀብት ያለው በመሆኑ የባለሀብቶችን ትኩረት እንደሚስብ ይጠበቃል፡፡ በየክልሉ ንግድና ኢንቨስትመንት ቢሮ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ፕሮሞሽን፣ ፈቃድና መረጃ ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ይደነቅ ወልደሰንበት፣ ስለክልሉ የኢንቨስትመንት ሀብትና የዘርፉ የሥራ እንቅስቃሴዎች፣ በተለይም ባለፉት ስምንት ወራት በክልሉ ስለነበረው የኢንቨስትመንት ስራ፣ በተለይ ለ‹‹አዲስ ዘመን›› ጋዜጣ የሰጡትን ማብራሪያ ይዘን ቀርበናል ፡፡

## የክልሉ የኢንቨስትመንት አቅም

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የበርካታ ሀብቶች ባለቤት ነው፡፡ ክልሉ ዓመቱን ሙሉ ዝናብ ያገኛል፡፡ በተፈጥሮ ሀብትም ታድሏል፡፡ በቡና መገኛነቱ የሚታወቀው ክልሉ፣ በተለያዩ ዘርፎች ለኢንቨስትመንት የሚሆን እምቅ የሆነና ገና ያልለማ አቅም አለው፡፡ ዓመታዊ ሰብል፣ ቡናና ቅመማ ቅመም፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ሌሎች የወጪ ንግድ ምርቶች (Export ltems)፣ ኢንዱስትሪ እና አገልግሎት ዘርፎች በክልሉ በኢንቨስትመንት ለመሰማራት የሚያስችሉ ሀብቶችና የምጣኔ ሀብት መስኮች ናቸው፡፡

በክልሉ ከፍተኛ የማዕድን ሀብት ያለ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ማዕድን ለማዕከላዊ ገበያ ከሚያቀርቡ የሀገሪቱ አካባቢዎች መካከል አንዱ ሆኗል፡፡ ወርቅ፣ የድንጋይ ከሰል እና ብረት ከማዕድናቱ መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ክልሉ በአዲስ መልክ የተደራጀ በመሆኑ ያሉትን የማዕድን ሀብቶች ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በስፋት በማጥናት ለኢንቨስትመንት ዝግጁ የሚያደርግ ይሆናል፡፡ እስካሁን በተደረገው ማጣራት የታወቀና ባለሀብቶችን የሚጠብቅ ከ150ሺ ሄክታር በላይ መሬት አለ፡፡

## የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችና የባለሀብቶች ተሳትፎ

ባለሀብቶች በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሰማራት ፍላጎት እያሳዩ ናቸው፡፡ ክልሉ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ የተሰሩት የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ስራዎች ባለፉት ወራት በክልሉ የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ በክልሉ ከ150 በላይ የሚሆኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፈቃድ ተሰጥቷቸው በተለያየ የትግበራ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በግብርና፣ በአምራችና እና በአገልግሎት ዘርፎች የተሰማሩ ሲሆን፣ ከሦስት ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታልም አስመዝግበዋል፡፡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶቹ ከ45ሺ በላይ ጊዜያዊና ከ20ሺ በላይ ቋሚ የስራ እድሎችን የሚፈጥሩ ይሆናል፡፡

ባለፉት ስምንት ወራት ከአንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ላስመዘገቡ 89 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን፣ ወደ ስራ ሲገቡ ከ47 ሺ በላይ (12ሺ ቋሚ እና 35ሺ ጊዜያዊ) የስራ እድሎችን እንደሚፈጥሩ ይጠበቃል፡፡

በክልሉ በኢንቨስትመንት ስራ ላይ ከሚገኙት ባለሀብቶች መካከል አብዛኞቹ በግብርና ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ናቸው፡፡ ክልሉ ለሰብል ልማት ምቹ ስነ ምኅዳር ያለው በመሆኑ በተለይ በዓመታዊ ሰብል፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በወጪ ንግድ ምርቶች (ቡናና ቅመማ ቅመም) እና በበጋ መስኖ ልማት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች ብዙ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአምራች እና በአገልግሎት ዘርፎች ኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሀብቶችም አሉ። በክልሉ በኢንቨስትመንት ስራ ላይ ተሰማርተው ከሚገኙት ባለሀብቶች መካከል አብዛኞቹ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ናቸው፡፡ ከሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ጋር በሽርክና የሚሰሩ የውጭ ባለሀብቶችም አሉ። ፕሮጀክቶቹ አቅማቸው ታይቶና በቴክኒክ ኮሚቴ ተገምግሞ አስፈፃሚው አካል ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ወደ ስራ እንዲገቡ እየተደረገ ነው፡፡

ለባለሀብቶች ጥሪ ተደርጓል፤ ባለሀብቶችን ለመቀበል በዞን የአስተዳደር መዋቅሮች አማካኝነት ግንዛቤ እንዲፈጠር ተደርጓል፡፡ ባለሀብቶች ወደ ክልሉ ሲመጡ ያለምንም መስተጓጎል ወደ ስራ እንዲገቡ በየጊዜው ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ የባለሀብቶች ጥያቄዎች በአጭር ጊዜ ምላሽ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ባለሀብቶች ምንም ዓይነት የቢሮክራሲ ችግር ሳይገጥማቸው ወደ ስራ እንዲገቡ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ለግብርና ዘርፍ ልማት ከፍተኛ አቅም ካላቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች አንዱ በመሆኑ፣ ክልሉ ለግብርና ኢንቨስትመንት ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ክልሉ በዘርፉ ያለውን አቅም የማስተዋወቅ፣ ባለሀብቶችን በፍጥነትና በጥራት የማስተናገድ፣ ጥሩ ፈፃሚዎችን የመሸለም፣ ችግሮችን በፍጥነት በመገምገም የእርምት እርምጃዎችን የመውሰድ እና ክትትሎችንና ድጋፎችን የማድረግ ተግባራት የዚህ ትኩረት ማሳያዎች ናቸው፡፡

## የመሰረተ ልማት አቅርቦት

ክልሉ በበጋም ሆነ በክረምት ወቅቶች አብዛኞቹን አካባቢዎቹን የሚያገናኙ መንገዶች አሉት፡፡ ውስን ከሆኑ ቦታዎች በስተቀር አብዛኞቹ የክልሉ አካባቢዎች የመንገድ መሰረተ ልማት አላቸው፡፡ በክልሉ ከሚገኙት አስፋልት መንገዶች በተጨማሪ በሁሉን አቀፍ የመንገድ ተደራሽነት መርሃ ግብር (URAP) የተሰሩ መንገዶችም የኢንቨስትመንት ፍሰቱን ለማሳለጥ ሁነኛ ግብዓት ሆነው ያገለግላሉ፡፡ የስልክ አገልግሎትም በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ተደራሽ ነው፡፡ በኃይል አቅርቦት ረገድ ግን ክፍተቶች ይስተዋላሉ፡፡

አዳዲስ የመንገድ ግንባታዎችን ጨምሮ በፌደራል መንግሥትና በክልሉ መንግሥት ተጨማሪ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ስራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። የክልሉ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ እየተሻሻለ ነው። አውሮፕላን ማረፊያዎችም እየተገነቡ ነው፡፡ ይህ የመሰረተ ልማት አቅርቦት መሻሻል ደግሞ ለባለሀብቶች መነቃቃትን እየፈጠረና የክልሉ የኢንቨስትመንት ዘርፍ እንዲያድግ እያደረገ ነው፡፡

## የሰላምና ፀጥታ ጉዳዮች

ሰላምና ፀጥታን ማስጠበቅ ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታዎችን ከሚፈጥሩ ግብዓቶች ዋነኛው እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ክልሉ ከተመሰረተ ወዲህ የሰላምና ፀጥታ ጉዳዮችን በቅርበት በመከታተል፣ ለሚፈጠሩ ችግሮች ዘላቂ ምላሽ ለመስጠት ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ቀደም ሲል ችግሮች ሲፈጠሩ በፍጥነት ተደራሽ የመሆን ክፍተቶች ነበሩ፡፡ እነዚህን ክፍተቶችን ለማረም በተከናወኑ ስራዎች የፀጥታ ስጋቶችን ማስወገድ ተችሏል፡፡ በሰላምና ፀጥታ መደፍረስ ምክንያት ስራ አቋርጠው የነበሩ ባለሀብቶች በአሁኑ ወቅት ተመልሰው ስራቸውን መቀጠል ችለዋል፡፡ በዚሁ ምክንያት ቀደም ሲል ለኢንቨስትመንት ተመራጭ ያልሆኑ አካባቢዎች ጭምር የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች እየቀረቡባቸው ይገኛሉ፡፡ ሰላምና ፀጥታን የማስፈን ተግባር ከክልሉ መንግሥት ቀዳሚ አጀንዳዎች መካከልም አንዱ ነው፡፡

## የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች

ክልሉ የባለሀብቶችን ፍሰት ለመጨመር የሚያደርጋቸው ማበረታቻዎች በአዋጅና በመመሪያ በተደነገጉ የማበረታቻዎች (lncentives) አሰጣጥ መሰረት የሚፈፀሙ ይሆናል፡፡ ባለሀብቶችን በቁጥርም ሆነ በጥራት ለማብዛት የሰላምና ፀጥታ፣ የቢሮክራሲ እንዲሁም የመሰረተ ልማት ችግሮችን ከመፍታት በተጨማሪ፤ በሕግ ማዕቀፍ የተቀመጡ የማበረታቻ ስልቶችን መሰረት በማድረግ ትልቅ አቅም ያላቸውና በቁጥር የበዙ ባለሀብቶች ወደ ክልሉ ገብተው በኢንቨስትመንት ላይ እንዲሰማሩ ጥረት ያደርጋል፡፡ ቦታዎችን አዘጋጅቶ ለባለሀብቶች ማቅረብን ጨምሮ ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ተግባራትን ያከናውናል። ባለሀብቶች በፍጥነት ወደ ስራ እንዲገቡ ቅድመ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ ባለሀብቶች የምርት ስራቸውን ሲጀምሩ ክልሉ ተጨማሪ መሬት በማቅረብ ስራቸውን እንዲያስፋፉ ያበረታታል፡፡

## ኢንቨስትመንትና ማኅበረሰባዊ ተጠቃሚነት

የክልሉ መንግሥት ባለሀብቶችን ወደ ክልሉ ሲያስገባ ባለሀብቶች በተለያዩ መንገዶች የአካባቢውን ማኅበረሰብ ተጠቃሚ እንዲያደርጉ በማሰብ ነው። ማኅበረሰቡ ከኢንቨስትመንት ስራዎች በስራ እድል ፈጠራ፣ በምርትና አገልግሎት አቅርቦት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግርና በገበያ እድል ተጠቃሚ እንዲሆን ይጠበቃል። ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ስራዎቻቸውን በሚሰሩባቸው አካባቢዎች የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ተግባራትን ስለሚያከናውኑ የአካባቢው ኅብረተሰብ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

## የዘርፉ መሰናክሎች

ቀደም ሲል በነበሩ የሰላምና ፀጥታ ችግሮች ምክንያት የተፈጠሩ ስጋቶች ብዙ የኢንቨስትመንት ጥያቄዎችና ፕሮጀክቶች በጥቂት የክልሉ አካባቢዎች ላይ ብቻ እንዲከማቹ መንስዔ ሆነው ነበር፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግም የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ሰፋፊና ለም መሬት ወዳለባቸው አካባቢዎች እንዲሰራጩ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ ክልሉ ከተመሰረተ ገና አዲስ በመሆኑ የኢንቨስትመንት ስራዎችን ለማሳለጥ አልፎ አልፎ የሚያጋጥሙ የሎጂስቲክስ እጥረቶች አሉ፡፡ የኢንቨስትመንት ስራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ አደረጃጀቶችን የማጠናከርና ግብዓት የማሟላት ስራ እስከታችኛው መዋቅር ድረስ እየተሰራ ይገኛል፡፡

## ቀጣይ እቅዶችና የትኩረት አቅጣጫዎች

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል አስደናቂ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ልምላሜና ሀብት ያለው በመሆኑ ይህን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ እቅድ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ክልሉ ሰፊና ለም መሬትና ውሃ ያለውና በበጋም ሆነ በክረምት መልማት የሚችል በመሆኑ የግብርና ኢንቨስትመንት ስራው በስፋት ተጠናክሮ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ በክልሉ በማዕድን ዘርፍ ያልታወቁ ሀብቶች ጭምር ስላሉ ባለሀብቶችን በብዛት በመጋበዝ፣ ሀብቱን በዘመናዊ መንገድ ጥቅም ላይ በማዋል ሕዝብንና ሀገርን ተጠቃሚ ለማድረግ ሰፊ ርብርብ ይደረጋል፡፡

ቡናና ቅመማ ቅመምን ጨምሮ በሌሎች የወጪ ንግድ ምርቶች ዘርፍ ያለውን አቅም ለመጠቀም ሰፋፊ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ ክልሉ አራት ዋና ከተሞች ያሉት ስለሆነ በየከተሞቹ የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን በማዳረስ የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ታቅዷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የክልሉን አቅም በመጠቀም የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ለማሳደግና ኢንዱስትሪ መር ምጣኔ ሀብታዊ ሽግግርን ለማሳካት አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

## ጎሜ

# «ጌታ ሆይ! ከወንበዴዎች ከልለኝ»

**ግርማ መንግሥቴ**

ዛሬ እያተራመሰን፣ እየዋጠን፣ እንደ ጭራቅም እያስፈራን . . . ስላለው ውንብድና እናወራልን። በዚህች አምድ የዘመኑ የህልውና ስጋት ስለሆነው የውንብድና ወንጀል እንነጋገራለን። የወንጀሉን ወሰን ዱካ (ከየት ተነስቶ እዚህ ስለ መድረሱ) ጠቆምቆም እናደርጋለን። እንዲሁም፣ በውንብድና ወንጀል አሁናዊ ይዞታ፤ ስለ "ሿሿ" አነሳስና አስተዳደግ "እነሆ በረከት" እንላለን። ሁሉንም "ለጠቅላላ እውቀት" ለጥንቃቄ በሚበጅ መልኩ እያሰናሰልን እናቀርባለን። እንቀጥል።

ውንብድና በወንጀል ሕጉ ስድስተኛ መጽሐፍ፣ በምዕራፍ ሁለት ከተመለከቱት በሚንቀሳቀስ ንብረት ላይ ከሚፈፀሙ ወንጀሎች መካከል አንዱ፤ የወንጀሉ ምንነትም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 670 በዝርዝር የተመለከተ ሲሆን፤ እሱም

ማንኛውም ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውን ተንቀሳቃሽ እቃ ለመውሰድ እንዲያመቸው ወይም በሚወስድበት ጊዜም ሆነ ከወሰደ በኋላ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስቀረት ሲል በሌላ ሰው ላይ የኃይል ድርጊት ወይም ከባድ የሆነ የማንገላታት ተግባር ወይም ከባድ ዛቻ የፈፀመ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ይህን ሰው መከላከል እንዳይችል ያደረገ እንደሆነ የውንብድና ወንጀል እንደፈፀመ መደንገጉ ነው።

እንዳው ለነገሩ ተግባሩ ከሕግ አኳያም (ለምሳሌ በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ መመልከት ይቻላል) የሚያስጠይቅ መሆኑን ለማመልከት እንጂ በዚህ በኩል ልንገፋበት ፈልገን አይደለም፤ ይልቁንም ዓለም አቀፍ ይዞታውን ትንሽም ቢሆን ነካ ነካ እናድርግ።

በፈረንጆቹ በሁለት ቃላት (banditry እና brigandage) በሚገባ የሚታወቀው ውንብድና አድማሱ ከዚህ በመለስ የሚባል፤ ጥፋቱም በአንድ ሁለት ቆጠራ የሚያልቅ አይደለም። ወጪውም (የሚያስወጣው) ከማናቸውም እየናረ ሲሆን ጉዳቱም ሕይወትን እስከ ማሳጣት ድረስ እየዘለቀ ነው። ይህ ሁሉ ታዲያ፣ ገና በጠዋቱ፣ በጨቅላነቱ በአግባቡ ባለመያዙ እና በስመ "ዲሞክራሲያዊ መብት" በእንጭጭነቱ ሊቀጭ ባለመቻሉ የመጣ ነው ይባላል።

ድሮ ድሮ ውንብድና "የባህር ላይ ውንብድና" በሚል በባህር ላይ ወንበዴያዊ ማንነቱ ነበር የሚታወቀው። ይህንን ደግሞ የሚያውቁት (ግሬግ ቤየር በማርች 13፣ 2023 ጥናታቸው እንደሚነግሩን) በተለይ በአራቱም የዓለማችን ማእዘን ይንቀሳቀሱ የነበሩት ሲራራ ነጋዴዎች ናቸው።

ይህ የቀድሞው ውንብድና (Piracy) በካሬቢያን አካባቢ ያቆጠቆጠ ሲሆን፣ ህልውናውን በባህር ፖርቶች (pirate seaports) ላይ አርጎ በጃማይካው ፖርት ሮያል (Port Royal)፣ በሀይቲው ቶርቹጋ (Tortuga)፣ በሀማሱ ናሳው (Nassau) ላይ ሲሞላቀቅና ሲንደላቀቅ ነው የኖረው ነው የሚሉት - ስለ እሱ (የወንበዴዎቹን (pirates) ታሪክ ጨምሮ) ታሪክ የሰነዱ ሰነዶች።

የዚህ፣ ስፔንና ፖርቹጊዝ አሜሪካንን በቅኝ በያዙበት ወቅት የተፈጠረ ውንብድና ("ዘረፋ" የሚሉትም አሉ) ወርቃማ ዘመን (The Golden Age of Piracy) በዘመናት ተቀንበቦ የሚታወቅ ሲሆን እሱም ከ1650 እስከ 1726 ያለው፤ በዚሁ ወቅት በተግባሩ ላይ ተሰማርተው የነበሩት ወንበዴዎች (pirates) 5000 እንደ ነበሩ በደማቁ ተፅፎ ይገኛል። መናኸሪያ ስፍራውም ካሬቢያን፣ ምስራቃዊው ሰሜን አሜሪካ፣ ምእራብ አፍሪካን ኮስት፣ ኢንዲያን አሽን አካባቢዎች እንደነበሩም እንደዛው።

ለጠቅላላ እውቀት ይህንን ያህል ወደኋላ ከሄድን ይበቃልና ወደ "ዛሬ"ያችን፣ ወደ ራሳችን ጉዳይ እንመለስ።

ጥያቄው "ዛሬስ?" በየጓዳ ጎድጓዳው፣ ደበበ እንዳለው በየ"ጓጥ ስርጓጉጡ" ከማለትም ባለፈ በየአደባባዩ፣ በየታክሲና አውቶሞቢሉ፣ በየሕዝባዊ ድርጅቶችና ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የእምነት ተቋማትና ገበያ ማእከላት ወዘተ . . . ሁሉ ውንብድና ጥግ ድረስ አለ። የኢንተርኔቱንማ ዝም እንጂ ቃላት አይገልጹትም።

ይህ አይደለም የሚገርመው፣ የሚገርመው "ውንብድናን እንዋጋለን"፣ "ውንብድናን እናጠፋለን . . ." በሚሉ ወገኖች ውስጥ ሁሉ ውንብድና ከጫፍ እስከ ጫፍ መኖሩ ነው።

ያኔ፣ ዓለም በየባህሩ ላይ እንዲያ ሲሰቃይ፣ እኛ "አትሳቁ በጥርስ ይደርሳል" የሚባለውን ረስተን በእነርሱ እንስቅ ነበር አሉ። ጥያቄያችንን እንድገመውና "ዛሬስ?" ዛሬ እያለቀስን እንዳይሆን የብዙዎች ስጋት ነው።

ጉዳዩን ሰፋ አድርገን እንየው ከተባለ አገራትን መጠቃቀስ የግድ ይሆናልና ማሳያ እንጥቀስ።

በዓለማችን በዘመናዊው (ተራ) ውንብድና ከፍ ብላ የምትታይ፣ ድምፅዋ ጎላ ብሎ የሚሰማ ከወደ አፍሪካ - ደቡብ አፍሪካ ናት። በደቡብ አፍሪካ ውንብድና የእለት ተእለት ተግባር ሲሆን እጅግ ከመለመዱ የተነሳ ተደራጅቶ ራስን መጠበቅ "ዘመናዊ" አሰራር እስከ መሆን ሁሉ እየደረሰ ነው። ጉዳዩን ጉዳዩ ብለው የሚከታተሉት እንደሚነግሩን በአገሪቱ ትልቁ ከተማ፣ ጆሃንስበርግ ደግሞ የባሰ ነው። ወንበዴዎች በጠራራ ፀሐይ አንገት አንቀው ኪስ እስከመበርበር ይደርሳሉ። መሐል ከተማ ካልሆነ በቀር ከተሞቹ ዳርቻ በሰላም መለስ ቀለስ ማለት ሁሉ አይታሰብም።

ናይሮቢ መንገድ ላይ ትንሽ ገንዘብ ይዞ መቁጠርና መቀባበል ማሰቡ ራሱ ከእብደት ሁሉ ሊያስቆጥር ይችላል። የሸቀጥ ሱቆች ሳይቀሩ በብረት የታጠሩ ናቸው። ካምፓላ መንገድ ላይ ስልክ እያወሩ መሔድ የቅብጠቶች ሁሉ ቅብጠት ሲሆን፤ ናይጄሪያና ሌሎችም ጋ ቢብስ እንጂ ያነሰ አይደለም።

ከ20 አመታት በላይ ያለ መንግሥት የከረመችው ሶማሊያ ውስጥ ያለውን ያው እናውቀዋለንና እንለፈው። ይህ ሁሉ ሲሆን፣ ያኔ እኛ በእነሱ እንስቅ ነበር ነው የሚባለው። ከአፍሪካ እንውጣ።

ከላይ፣ በመግቢያ አንቀፆቻችን ጠቆም ለማድረግ እንደሞከርነው፣ በ17ኛውና በ18ኛው መቶ ዘመን የባሕር ላይ ውንብድና በተለይ በዌስት ኢንዲስና በአሜሪካ ድንበር አካባቢ "የባሕር ላይ መቅሰፍት" ሆኖ ነበር። ዛሬስ?

በ1994 የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያሳየው በዩናይትድ ስቴትስ በሚገኙ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ዓመፅና ውንብድና ዋነኛ ችግር ሆኖ ከመገኘቱም በላይ ከፍተኛ የገንዘብ ወጪን እያስከተለ ያለ የወንጀል ተግባር ሲሆን፣ ባለፈው ዓመት ብቻ ከፍተኛውን ወጪ ላፍ ያደረገው ይሄው ወንበዴዎችን የማደንና ንፁሃንን የመታደግ ስራ ነበር። ያኔም እኛ ውንብድናን በሩቁ ነበር የምንሰማው።

ከላይ ባደረግነው ምጥን ገለፃ ምናልባት ያጋነንን የመሰለው ገራገር አንባቢ ከዚህ በኋላ አብሮን የሚቆይ ከሆነ እውነቱን ይረዳዋል።

የዛሬይቱ ኢትዮጵያና እኛ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያዊያን እያጋጠሙን ያሉት ችግሮች ከዚህ በፊት አጋጥመውን የማያውቁ ናቸው። ምናልባት እኛ አጋጥመውን የምናውቃቸው "ቤት ሰርሳሪዎች የእንቶኔን ቤት ሰርስረው በመግባት ዘረፉ"፣ "እንቶኔን ማታ አምሽቶ ሲመጣ ማጅራት መቺዎች ዘረፉት (ወይም ገፈፉት)" የሚሉ አይነት አገላለፆችና የሌብነት ተግባራት ነበሩ። ዛሬስ?

ድሮ፣ ብዙ ሱቆች ሸቀጦቻቸውን በፈለጉት መጠንና አይነት በመስታወት ማሳያ ውስጥ ያስቀምጣሉ፤ ሰዎች ከባንክ ገንዘብ ተሸክመው መንገድ ላይ በነጻነት ይንቀሳቀሱ ነበር። ማታለሎች፣ ማጭበርበሮች እና ስርቆቶች፤ እንዲሁም ኃይል የቀላቀሉ ዝርፊያዎች ቢኖሩም፣ የፀጥታ ኃይል ባለበት፣ ቀንና ሰው በተሰበሰበበት ይፈፀሙ ዘንዳ አይታሰብም ነበር አይደል ?

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ (በተለይ በከተሞች) እነዚህ ሁሉ ተረት ሆነዋል። ተረት ሆነውም በምትካቸው አደገኛ ወንበዴዎችና የውንብድና ተግባራት ተተክተዋል። እስኪ እንያቸው።

በዛሬይቱ አትዮጵያ ያሉት ተጨባጭ የውንብድና ተግባራት በሁሉ ነገራቸው እየተሻሻሉ፣ እየደረጁ . . . በመሄድ ላይ ያሉ ሲሆን፣ ትጥቅና ስንቅ አደራጅተው እስከ መንቀሳቀስ ድረስ ዘልቀዋል ነው የሚባለው።

በተለይ በመዲናዋ በአዲስ አበባ ውስጥ ያለው

> **በየአደባባዩ፣ በየታክሲና አውቶሞቢሉ፣ በየሕዝባዊ ድርጅቶችና ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የእምነት ተቋማትና ገበያ ማእከላት ወዘተ . . . ሁሉ ውንብድና ጥግ ድረስ አለ። የኢንተርኔቱንማ ዝም እንጂ ቃላት አይገልጹትም። ይህ አይደለም የሚገርመው፣ የሚገርመው «ውንብድናን እንዋጋለን»፣ «ውንብድናን እናጠፋለን . . » በሚሉ ወገኖች ውስጥ ሁሉ ውንብድና ከጫፍ እስከ ጫፍ መኖሩ ነው**

የወንበዴዎች ይዞታ በቀላሉ የሚደፈር የማይመስል ሲሆን፣ ተደራጅተውና የሞባይል ቴክኖሎጂን በመጠቀም ከባድ የውንብድና ወንጀል በመፈፀም የሕዝብን ሰላም እያወኩት እንደሆነ እየሰማን ያለነው "14 የሽብር ቡድን አባላትን ባካሄድኩት ከፍተኛ ኦፕሬሽን በቁጥጥር ሥር አውያለሁ" ከሚለው አፊስ ነውና ጉዳዩ "አሳሳቢ" በሚለው ብቻ የሚታለፍ ሳይሆን "አስደንጋጭ" የሚለውም ሊታከልበት ይገባል።

"አደገኛ"፣ "አስደንጋጭ"፣ "አሳሳቢ" . . . ወዘተ የሚሉ አጎላማሾች መጠቀሙ ለምን አስፈለገ ለምንል፣ አስፈላጊነታቸው፤

ወንጀሉን ለመፈፀም ይጠቀሙበት የነበረ አንድ ሽጉጥ፤ ሶስት የብረት መቁረጫ፣ አንድ የብረት መፈልቀቂያ እና ሁለት ከፍተኛ ኃይል ያለው የፓውዛ መብራት፤ እንዲሁም፣ በርካታ ሐሰተኛ መታወቂያዎችን ጨምሮ የሚንቀሳቀሱበት በአንዱ ኮድ 1-...... በሆነ ሚኒባስ ታክሲ . . . መሆናቸውን ስንገልጽ በሀዘን ነው።

ዛሬ በኢትዮጵያ "ዩኒፎርም የለበሱ" መኪና እያስቆሙ የፈለጉትን ይቀበላሉ። መንገድ ላይ ደኅንነት እናስከብራለን በሚሉ ወጣቶች እንዲቆሙ ይደረጋሉ፤ ይፈተሻሉም። አንዳንድ አካባቢዎች ጉልበተኛ በሆኑ ቡድኖች በሕጋዊ መንገድ የተሠሩ ቤቶች ይፈርሳሉ። ወደ አንዳንድ የአገሪቱ አካባቢዎች እህል እና ሸቀጥ ጭነው የሚጓዙ መኪኖች የሕግ አስከባሪ ባልሆኑ ሰዎች ተገደው እንዲቆሙ ከተደረጉ በኋላ ይፈተሻሉ፤ ይዘረፋሉም። መኪና ላይ የሚጫኑ ዕቃዎችን ለማውረድም ሆነ ለማውጣት ተመን አውጪዎቹ (ይህ አሁን የተሻሻለ ቢመስልም) በውንብድና ተግባራት የተሰማሩት መሆናቸው "አገር ያወቀው ፀሀይ የሞቀው" ከተባለ ቆየ።

ከላይ እንዳየነውና ከታችም እንደምናየው፣ በአዲስ አበባ ፈላጭ ቆራጭ የሆኑ ቡድኖች በመብቀል ላይ መሆናቸው እየተነገረ ይገኛል። ሰሞኑን ለጤናቸው የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የሚያደርጉ የከተማዋ ነዋሪዎች እንኳን ጠዋት ተነስተው ልምምድ ማድረግ ወደ እማይችሉበት ደረጃ እየተደረሰ ነው የሚባለው (ሰሞኑን አምስት የፌደራል ፖሊስ ልብስ ለብሰው "ነን" ባሉ ወጠምሾች የተዘረፉትን ልብ ይሏል)። ሌላም ሌላም የዝርፊያ አይነት በከተማችን ተስፋፍቷል።

"በራይድ ታክሲ የትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጡ ሹፌሮች ላይ የሚፈፀም ግድያንና የከባድ ውንብድና ወንጀልን በተመለከተ የተጣሩ [9] የምርመራ መዛግብትን በተመለከተ የተሰጠ"ን የፍትህ ሚኒስቴር መግለጫ ስንሰማ ያልተረበሸን ያለን ስለመሆናችን ምንም የተሰማ ወሬ የለም። "ምርመራቸው በተጠናቀቁና ክስ በተመሰረተባቸው መዝገቦች ላይ እንደታየው ቡድኑ ሶስት የሚሆኑ ሰዎችን በመግደል ሟቾች ሲያሽከረክሯቸው የነበሩትን ተሽከርካሪዎችንና ሌሎች ንብረቶችን የወሰዱ ሲሆን፣ በዚህም ሂደት ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ሕይወት ጠፍቷል።" በሚለውም ማን ያልተረበሸ፣ ግራም ያልተጋባ፣ ህልውናው አደጋ ላይ የወደቀ ያልመሰለው ማን አለ? የእነዚህ ሁሉ የውንብድና ተግባራት ውጤት ደግሞ ራይዶች ከሰፈራቸው ውጭ እንዳይሰሩ እያደረጋቸው ብቻ ሳይሆን፣ የከተማዋ የትራንስፖርት ተጠቃሚዎችም የሚያስፈልጋቸውን የትራንስፖርት አገልግሎት እያገኙ አይደለምና የወንጀል ድርጊቱ ያላንኳኳው በር የለም ማለት ይቻላል።

እዚህ ላይ፣ ከመሸ የማይኬድባቸው፣ ጭር ባለና በጠራራ ፀሐይ የማይታለፍባቸው፣ ዘወርወር ያሉ መንገዶች በመንገደኞች አለመደፈራቸው፤ እንዲሁም፣ ሌሎች መሰል ጊዜያትና አካባቢዎች ቅጥራቸው በየጊዜው የጨመረ ነው።

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ እንደነ ነፃነት መለሰ ጊዜ "ሿሿ" ለአረንቻታ ከመሰለን ተሳስተናል። "ሿሿ" ሰራኝ/ሰሩት/ሰራው/ሰሩን/ሰራችን . . . የሚለው የወንጀል ተግባር መግለጫ መደበኛ የቋንቋ አገላለፅ ውስጥ ከገባ ጊዜው ዛሬ ሳይሆን አስርት አመታትን ወደኋላው አድርጓል። ሌብነት፣ ማጅራት መቺ፣ ኪስ አውላቂ፣ ዘራፊ እና የመሳሰሉትን "ኧረ በስንት ጣእማቸው" መባል ከተጀመረ ቆየ። በታሪክ ከመቸውም ጊዜ በላይ የፀጥታ ኃይል አባላት አዲስ አበባ "ጌታ ሆይ ከወንበዴዎች ከልለኝ" የዘወትር ፀሎት ያህል ሲዘወተርባት ነው ውሎና አዳሯ።

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ እንደ ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ "በህግ አምላክ"፣ "በባንዲራው" . . . ይሰራል ብለው በተገኘው ጊዜና ስፍራ ጎምለል . . . ጎምለል እላለሁ ካሉ፣ የፖሊስን "ራሳችሁን ጠብቁ" ማሳሰቢያም ይሁን ማስጠንቀቂያ አልሰሙምና በዚሁ አጋጣሚ እንዲያነቡና እንዲሰሙ እንመክሮታለን።

ባጠቃላይ፣ ዓለም ተለውጣለች። ትለወጥ እንጂ ለውጡን በአግባቡ የያዙ አገራት የሉም ማለት አይደለም። መለወጥ መዝረፍ ወይም መዘረፍ ማለት አይደለም። መለወጥ ከለውጡ ጋር አብሮ በመለወጥና በመጓዝ የለውጡ አካል በመሆን ራስን፣ አካባቢንና አገርን ማዘመን ነው። ከዘመናዊነት መካከል ደግሞ አንዱ ሰላምና ፀጥታ ስለመሆኑ ከማንም ያልተሰወረ ነው። ከዘመናዊነት መካከል ሌላኛው የሰለጠነ ማህበረሰብ መፈጠር ነው። የሰለጠነ ማህበረሰብ መፈጠር ማለት ደግሞ እርስ በእርሱ የሚደጋገፍ፣ የሚከባበር፣ የሚፈቃቀር ... ማህበረሰብ ተፈጠረ ማለት ይሆናልና በዚህ ውስጥ ደግሞ ዘረፋ፣ ውንብድና፣ ሙስና . . . ምንም ቦታ አይኖራቸውም ማለት ይሆናል። ይህንን ሁሉ ስንል ግን የመንግስትና ፀጥታ ኃይሎችን የማይተካ ሚና ረስተን አይደለም።

**ሰላም!!!**

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# የበገና ጥበብ - የመንፈስ ሰላም ፤ የነፍስ ዝማሬ

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

‹‹በገና›› የአማርኛ ቃል ነው። በግዕዝ አጠራሩ ደግሞ ‹‹እንዚራ›› የሚል ስያሜ ተችሮታል። የቤተክርስቲያን ሊቃውንት እንደሚሉት ‹‹በገና›› ማለት ‹‹በገነ›› ከሚለው ግስ የተወረሰ ቃል ነው። በሌላ መልኩ ‹‹ወግሥ ወ መዝገበ ቃላት ሐዲስ ›› በሚለው የአለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋሰው ላይ ‹‹በገና›› ቃሉን በማጥበቅና በማላላት ሊሰጥ የሚችለው ትርጓሜ እንዲህ ተቀምጧል።

‹‹በገና›› በዕብራይስጥኛ ‹‹ናጌን›› በመባል ይጠራል። የዚህ ቃል ትርጓሜም ነዘረ፣ መታ፣ ደረደረ፣ እንደማለት ነው። በሌላ መልኩ ይኸው ቃል ጠብቆ ሲነበብ ነደደ፣ ተቆጣ የሚል ፍቺን ይይዛል። በአለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ መጽሐፍ ላይ በግልጽ እንደሰፈረው በገና በቁሙ ሲመነዘር መዝሙር እንደማለት ይሆናል።

በአባ ዮሐንስ ገ/እግዚአብሔር ትግርኛ አማርኛ መዝገበ ቃላት ላይ ደግሞ በገናን በጥሬው እንደነበረ ሆኖ ‹‹በገና›› ተብሎ ተተርጉሟል። የከሳቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ላይ የሰፈረው እውነታም የበገናን ትርጓሜ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል።

‹‹በገና በአሥር አውታር ጅማት በገናን ሰራ፣ ቃኘ፣ ደረደረ፣ ድምጽን እያጣራ፣ እያጣቀሰ፣ እየነዘረ፣ በገናን በገነ ማለት ነው። ‹‹በገነኛ ›› ማለት ደግሞ በገናውን የሚመታ፣ ዕውቀቱ ያለው፣ ደርዳሪውን ሰው ያመለክታል። በሌላ መልኩ በገነ ማለት አደረቀ፣ አቃጠለ፣ አነደደ የሚል ሀሳብን ይይዛል።

የዚህ ቃል ትርጓሜም ከበገና አካላዊ አሰራር ጋር የሚቀናጅ ነው። በገና ደረቅ በሆኑ ግብአቶች እንጨትና ቆዳ እንዲሁም በደረቅ ጅማት ይሰራልና……

ዕውቁ የበገና ደርዳሪ ዓለሙ አጋ እንደሚሉት ደግሞ ‹‹በገና›› የሚለው ቃል ‹‹ገና›› ከተሰኘው የእየሱስ ክርስቶስ ልደት ጋር የሚዛመድ ነው። ይህም ከመወለዱ ጋር ተያይዞ በዕለቱ ምስጋና የተደረደረበት መሳሪያ መሆኑን ያስታውሳል። የበገና ሌላው ፍቺ ‹‹ደረደረ›› እንደ ማለት ነው። በቃሉ ውስጥም ድርደራን፣ ምስጋናን ዝማሬን ይዋህዳል።

ብዙዎች በጥንት ጊዜ በገና ለነገስታት ፍላጎት ብቻ ይውል እንደነበር ያስባሉ። ይሁን እንጂ በገና ከፈጣሪ ለሰው ልጆች የተሰጠና ቅዱስ የሆነ የማመስገኛ ጥበብ መሆኑን በርካታ ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ።

በገና በተወጠሩ ክሮች የሚሰራ የኢትዮጵያ የሙዚቃ መሳሪያ ነው። ቁመቱ የረዘመ፣ ገበታው የሰፋ ቁመናም አለው። የላይኛው የአናቱ ክፍል ‹‹ቀንበር›› ወይም ‹‹ጋድም›› ይባላል። በዚህ ክፍል ላይ ያማሩ ጌጦችና መቃኛው ይቀመጣሉ። በቀኝና ግራ ምሰሶዎቹ የተወጠሩት ክሮች ከድምጽ ሳጥኑ /ገበቴው/ ጋር የተዛመዱ ናቸው።


በገና አስር የክር አውታሮችን የያዘ ነው። ብርኩማ፣ እንዚራ፣ መወጠሪያና መምቻ/ ድህንጻ / የተባሉት ክፍሎች በገናን ሙሉ ለማድረግ የሚያግዙ አካል ናቸው።

በገና የሚደረደረው በቤተክርስቲያን እንደመሆኑ የአፈጣጠሩ ይዘት በመንፈሳዊነት ምሳሌ ይመነዘራል። የሐይማኖት ሊቃውንት እንደሚሉት ከላይ ያለው ቀንበር /ጋድም/ እግዚአብሔር የበላይ መሆኑን አመላካች ነው። በቀንበሮቹ ላይ አጊጠው የተቀመጡት መስቀሎችም እግዚአብሔር በመስቀል ተሰቅሎ ፍቅሩን ስለመግለጹ ጠቋሚ ናቸው።

በስተቀኝ በኩል ያለው ምሰሶ እግዚአብሔርን የመውደድን ማሳያና የብሉይ ኪዳን ተምሳሌት ነው። በግራ በኩል ያለው ምሰሶም ሰውን የመውደድና የብሉይ ኪዳን ምሳሌ ተደርጎ ይወሰዳል። ዝቅ ብሎ ያለው የገበቴው አካልም ቅድስት ድንግል ማርያምን ይወክላል።

አውታሩ ሲመታ ድምጹ የሚወጣው ከገበቴው ክፍል ነው። ይህም ወልድ እየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ ቅድስት ማርያም የመወለዱን እውነታ ይጠቁማል። ይህ ገበቴ በሁሉም አቅጣጫ አንዳች ቀዳዳ የሌለው ፍጹም ድፍን መሆኑ ይታያል። ይህም የማርያምን የድንግልና ምስጥር ይጠቁማል።

ብርኩማው የሲና ተራራን አመላካች ምሳሌ ነው። ሙሴ በዚህ ተራራ አስርቱን ትዕዛዛት ከአምላኩ መቀበሉን ልብ ይላል። እግዚአብሔርና የሰው ልጅም




**በገና እንደሌሎች የዜማ መሳሪያዎች ጊዜና ቦታ ተወስኖለት በአግባቡ የተጠበቀ አልነበረምና በአንድ ወቅት «በመሞት» ላይ ያለ የሚል ስያሜ ተችሮት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በሀገራችን ብቻ የሚገኝ የዓለማችን ቅርስ ለመሆን ችሏል**

ልክ እንደመቃኘው በአምላኩ መንፈስ ሲቃኝ ጣዕም ያለው ሕይወት ይኖረዋል በሚል እሳቤ የበገናውን ጥዑም ዜማ ያስታውሳል።

በበገናው የታችኛው ክፍል የሚገኘው መወጠሪያም የሰው ልጅንና የምድርን ገጽታ የሚወክል ምሳሌን ይዟል። የሰው ልጅ የሁሉም ፍጥረታት የበላይ የሆነውን እግዚአብሔርን ሊያከብር የሚችለው በአስርቱ ትዕዛዛት በመመራት ነው። ይህም ከበገናው አናት ጀምሮ በታሰሩት አስር አውታሮች ተምሳሌትነቱ ተጠቅሷል።

በገና የጸሎትና የምስጋና ዜማ መሳሪያ ነው። መሳሪያውን ተቀምጦም ሆኖ ቆሞ መደርደር ይቻላል። እንደ ቅዱስ መጽሐፍ እውነታ በገናን ለመጀመሪያ ጊዜ የደረደሩት የላሜህ ልጅ የዩባል /ኢዮቤል/ ልጆች ነበሩ። አይነስውሩ አያታቸው ላሜህ በበረሀ ይጓዝ በነበረ ጊዜ አባቱ ቃኤል ከእሱ ተለይቶ በዱር በጫካው ይንቀዠቀዥ ነበር።

ላሜህ በመንገዱ ቅጠሎች የተንኮሻኮሹ፣ ቢመስለው አውሬ እንደመጣባቸው መስሎ ተሰማው። ወዲያው ስጋቱን መንገድ ይመራው ለነበረ ሰው ተናገረ። በዚህ ብቻ ዝም አላለም። ድንጋይ እንዲያቀብለው ጠየቀው።

የዓይኑ መሪ ወዲያው የጠየቀውን ድንጋይ ፈጥኖ ከእጁ አኖረለት። ላሜህ አልዘገየም። ድምጽ ወደሰማበት አቅጣጫ ድንጋዩን አርቆ ወረወረው። የተወረወረው ድንጋይ የአባቱን የቃየንን ግንባር መታና ገደለው። አባትም በልጁ ላሜህ እጅ ለሞት በቃ።

ላሜህ በአባቱ ላይ የሆነውን ሁሉ ባወቀ ጊዜ በመሪር ሀዘን ተደፍቶ አለቀሰ። አስቀድሞ አቤል በቀናተኛው ወንድሙ ቃየል ተገድሏል። የሚያውቁ ልጆቹም የቀደመውን ታሪክ አስታውሰው በእጅጉ አዘኑ። በቤተሰቡ ዘንድ የመረረው ለቅሶም ከደረቀ እንጨት በገና አሰርቶ ለመጀመሪያ ጊዜ በሀዘን ዜማ አስቆዘማቸው። የሀዘን ዜማው በበገና ድርደራ የታጀበ ነበር።

በኢትዮጵያ የበገናን አጀማመር በተመለከተ ትክክለኛው መረጃ አልተቀመጠም። ይሁንና የጅማሬው ምንጭ ከንጉስ ሰለሞንና ከኢትዮጵያዊቷ ንግስት ማክዳ /ዕሌኒ/ ልጅ ከቀዳማዊ ምኒልክ ታሪክ ጋር እንደየሚያያዝ ይገመታል። ቀዳማዊ ምኒልክ በአገረ እስራኤል ቆይቶ ወደ ኢትዮጵያ በተመለሰ ጊዜ የበገና መሳሪያ አብሮት እንደገባ ይታመናልና።

ኢትዮጵያዊው ካህን ማህሌተ- ቅዱስ ያሬድ በአምስቱ ጽዋዕተ ዜማዎቹ ተለይቶ ይታወቃል። ድጓ፣ ጾመድጓ ፣ ዝማሬ፣ መዋዕስት፣ ምዕራፍ እመመለሰ በተባሉት ዜማዎቹ በዓለም የዜማ ታሪክ ቀዳሚውን ድርሻ እንዲይዝም ሆኗል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንም፣ በህገ ልቦናና በህገ ኦሪት እግዚአብሔር ሲመሰገንበት የኖረውን የዜማ ዕቃዎችና ከቅዱስ ያሬድና ሌሎች ሊቃውንት ከአዲስ ኪዳን ጀምሮ የተላለፈውን የዜማ ሀብት በክብር ይዛ አቆይታለች። በብሉይ ኪዳን የዜማ መገልገያ ከነበሩት መሳሪያዎች መካከል አንዱ በገና እንደነበርም አበው ሊቃውንት ያስረዳሉ።

በገና እንደሌሎች የዜማ መሳሪያዎች ጊዜና ቦታ ተወስኖለት በአግባቡ የተጠበቀ አልነበረምና በአንድ ወቅት ‹‹በመሞት›› ላይ ያለ የሚል ስያሜ ተችሮት ነበር። ይሁን እንጂ በሀገራችን ብቻ የሚገኝ የዓለማችን ቅርስ ለመሆን ችሏል።

የበገና ጥንታዊ ዳራ ሲመረመር ታሪኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ ሲጠቀስ መቆየቱን ማረጋገጥ ይቻላል። በገና ለፈውስ፣ ለድህነት፣ ለማህበራዊና መንፈሳዊ አገልግሎቶች ሲውል ቆይቷል። ይህ የዜማ መሳሪያ ከሰው ልጆች ጋር ረጅም ዓመታትን የዘለቀ ሲሆን ሰዎች ደስታና ሀዘናቸውን የሚገልጹበት ዘመን ተሻጋሪ መሳሪያ ነው።

በዘመነ ኦሪት በገና ከእንቢልታ ተቀናጅቶ የቃል ኪዳኑን ታቦት ያጅብ ነበር። እስራኤላውያንም ጠላቶቻቸውን ድል በነሱ ጊዜ ለምስጋናና ውዳሴ ተጠቅመውበታል። ሐይማኖታዊ አስተምህሮቱ እንደሚጠቁመው በገና ፈጣሪን የማመስገኛ የዜማ መሳሪያ ነው።

በገና የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ከአቢዳር ቤት በሚመጣበት ጊዜ፣ በዳዊት ከተማ ገብቶ በድንኳን በኖረበት ወቅት፣ ንጉስ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ሰርቶ ባጠናቀቀበት ዘመንና እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን ድል በነሱ ጊዜ ሁሉ በአገልግሎት ላይ የነበረ የዜማ መሳሪያ ነው። ልበ -አምላክ ዳዊት በእግዚአብሔር ከተሰጠው ሰባት አይነት ሀብቶች መካከልም አንዱ እንደነበር በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጠቅሷል።

በሀገራችንም ከጥንት ጀምሮ በቤተመንግስት አካባቢ ንጉሳውያንና መኳንንቱ፣ በቤተክህነት ዘንድም ካህናትና ቀሳውስት ለመንፈሳዊ አገልግሎት ሲጠቀሙበት ቆይተዋል። ብዙዎች እንደሚሉት የበገና ዜማ የሚደርሰው ለጆሮ ብቻ አይደለም። ድምጹ ውስጥን የማረስረስ፣ መንፈስን የመመሰጥ ታላቅ ኃይል አለው።

‹‹አንገረ ፈላስፋ› የተባለው መጽሐፍ ስለበገና ዜማ ኃያልነት እንዲህ ሲል አስፍሯል። ‹‹በገና በተደረደረ ጊዜ አራቱ ባህርያተ ሥጋ ለሶስቱ ባህርያተ ነፍስ ይገዛሉ›› ሊቃውንት እንደሚሉትም ክፉ ድርጊቶች ሁሉ በሰው ልጆች ስጋዊ አካል ላይ የሰለጠኑ ናቸው። ከልብ ዘልቆ የሚገባው የበገና ዜማ ግን የስጋ ፈተናዎችን የማረጋጋት ኃይል አለው።

ንጉስ ሳኦል መንፈሱ በታወከ ጊዜ ቅዱስ ዳዊት በገናውን እየደረደረ በንጉሱ ውስጠት ያደረውን ክፉ መንፈስ እንዳወጣለት ይታወቃል።

ስለበገና ምንነት ቅርበቱ ያላቸው ሰዎች እንደሚሉት ደግሞ በገና ሲደረደር መንፈስ ይማረካል፣ ክፉ ስሜት ይሰደዳል፤ ተቅበዝባዥ ኃይል ይሰክናል። ይህ እውነታም የበገና ባህሪያት ዋና መገለጫ ሆኖ አሁን ድረስ በመልካም ተጽእኖው እንዲዘልቅ አስችሎታል።

መምህር ሲሳይ ደምሴ ገብረጻዲቅ የሲሳይ በገናና የዜማ መሳሪያዎች ተቋም ስራ አስኪያጅ ናቸው። በአንድ ወቅት ለአንድ ሬዲዮ ጣቢያ በሰጡት አስተያየት ስለበገና ኃያልነት እንዲህ ብለዋል። ‹‹ ሀብተ በገና እንጨት ጠርቦ፣ ቁርበት ገልቦ፣ ጅማት ወጥሮ መደርደር ሲሆን ሀብተ ፈውስ ደግሞ በገናውን እየደረደሩ ድውይን መፈውስ ነው ››

ንጉስ ዳዊት ከብላቴናነቱ ጀምሮ በአምላኩ የተወደደና የተመረጠ ነበር። ዳዊት በገናን መልካም አድርጎ የመደርደሩ እውነትም በሰው ዘንድ ጭምር እንዲወደድ አድርጎታል። ንጉስ ሳኦልን ክፉ መንፈስ ባስጨነቀው ጊዜ የሳኦል ባሪያዎች በገናን በመደርደር ከክፉ መንፈስ መላቀቅ እንደሚቻል ያምኑ ነበር። ይህን ሀቅም ለንጉሱ በማሳመን በበገና እንዲፈወስና ውስጠቱ በበጎ እንዲማረክ ይመክሩት ነበር።

በገና ከአምስት ሺህ ስምንት መቶ ዓመት ዕድሜ በላይ እንዳስቆጠረ ይነገርለታል። በነዚህ ዘመናት ሁሉ ያገለግል የነበረው ፈጣሪን ለማመስገኛነት ብቻ ነው። በቤተክህነትና ስልጣን ባላቸው የቤተመንግስት ሰዎች እጅ ተከብሮ የመቀመጡ ሚስጥርም አብሮት የቆየው ክብርና ታላቅነት ስለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የጎንደሯን እቴጌ ምንትዋብን ጨምሮ አጼ ቴዎድሮስና አጼ ዮሀንስ አጼ ምኒልክና ፣ እቴጌ ጣይቱ ፣ እንዲሁም የአጼ ኃይለስላሴ አባት የነበሩት ራስ መኮንን የታወቁ በገና ደርዳሪዎች እንደነበሩ ይነገራል። በተለይ አጼ ቴዎድሮስ የዓለም ከንቱነት ሲሰማቸው፣ እቴጌ ተዋበችን ሲያስታውሱና በሀዘን ሲቆዝሙ ማረፊያቸው በገና እንደነበር ይነገርላቸዋል።

የበገና ግጥሞች የተለዩ ናቸው። በሌሎች የሙዚቃ መሳሪያዎች የተለመዱ አይነት ዜማ የላቸውም። ስንኞቹ ታስበውባቸው የሚጻፉና አእምሮ ላይ የተለየ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ናቸው። በገና በሚደረደር ጊዜ ‹‹ውስጠት ይቀየራል፣ መንፈስ ይረጋጋል፤ ለጸሎት ያበረታል›› የሚሉ ብዙ ናቸው።

በገና በአብዛኛው ጾምና የንስሀ ጸሎት በሚያዝበት ጊዜ የሚደረደር ኃያል መሳሪያ ነው። ታቦታትን ለማጀብም ጭምር ያገለግላል። በተለይ በሕዝበ ክርስቲያኑ ዘንድ ታላቁ ዓቢይ ጾም /ሁዳዴ/ ገብቶ ፋሲካ እስኪሆን ድረስ የበገና ድርደራዎች ጎልተው ይሰማሉ።

ብዙዎች እንደሚስማሙበት የበገና ድምጻት በተለየ ስሜት ውስጠትን ይቀይራል። መንፈስን ያድሳል። በርካቶች ለጾምና ጸሎት የሚጠቀሙበት፣ ከፈጣሪያቸው በተለየ የሚገናኙበት ኃያል የዜማ መሳሪያ ነው።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ጎዳና የወጡ ወገኖች መበራከትና የመፍትሄ እርምጃዎቹ

**ሰላማዊት ውቤ**

አላሮ ጳውሎስ የ10 ዓመት ታዳጊ ነው።ከአላባ አዲስ አበባ ከመጣ ሁለት ዓመት እንደሆነው ይናገራል።ሆኖም እስከ አሁን የሚያድረው ጎዳና ላይ ነው።ሰሞኑን ዝናብ ስለጣለ አስፋልት ኮሪደር ላይ አብረውት ከሚያድሩት ሌሎች ልጆች ጋር ቤሄራዊ ቲያትር አካባቢ ማደር ጀምሯል።እዚህ መኪና ላይ ይለምናሉ።“ ከሆቴል ቤት ትርፍራፊ (ቡሌ) ይበላሉ።ነገር ግን የሚሰራ ነገር አግኝተው ገንዘብ ከሌላቸው ሳይበሉ ሊያድሩ ይችላሉ። አሁን ታዳጊ አላሮ ወደ አላባ መመለስ ይፈልጋል።

“ተወልጄ ያደኩትና ነዋሪነቴ እዚሁ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው” ያሉን ወይዘሮ ቀለሟ ወይሶ ሌላዋ ጎዳና የወጡ የሦስት ልጆች እናት ናቸው።ጎዳና ለመውጣታቸው ዋናው ምክንያት ደግሞ የኑሮ ውድነቱን ነው።ልጆቻቸውን ያለ አባት ነው የሚያሳድጉት እነሱን ለማስተዳደር ይሰሯቸው የነበሩት ብዙ የጉልበት ሥራዎች አሁን የሉም፤ እንጀራና ዳቦ እየጋገሩ ገበያ አውጥቶ መሸጡ በዋናነት ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩበት የገቢ ምንጫቸውም ነበር።ስንዴና ጤፍ እየተወደደ በመምጣቱ ግን ሊያዋጣቸው ባለመቻሉ ትተውታል።በዚህ ምክንያት ደግሞ ለተከራዩት የግለሰብ ቤት ኪራይ መክፈል ቀርቶ ለልጆቻቸው የሚሰጡት ቁራሽ ሲያጡ ወደ ጎዳና ወጥተዋል።

በአሁኑ ወቅት በተለይ በመዲናችን አዲስ አበባ እነዚህ ብቻ ሳይሆኑ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለያዩ ገፊ ምክንያቶች ወደ ጎዳና የወጡበትና እየወጡም ያሉበት ሁኔታ አብዝቶ ይስተዋላል። የሴቶችና የማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ለኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት ባቀረበበት ወቅት ይሄንኑ እውነታ አረጋግጧል።በጉዳዩ ዙርያ ያነጋገርናቸው የሴቶችና የማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ እታገኝ አሰፋ እንደገለፁልን በተለይ በመዲናችን አዲስ አበባ በርካታ ሰዎች ወደ ጎዳና መውጣት እውነትነን ያለውና በእጅጉ አሳሳቢ የሆነ ጉዳይ በመሆኑ ሚኒስቴር መሥርያ ቤቱም በትኩረት እየተሰራበት ነው።ሴቶች፤ ወጣቶች፤ አረጋዊያን፤ ሕፃናት፤ የአካል ጉዳተኞች ሁሉም ዓይነት የሕብረተሰብ ክፍሎች አሁን ላይ በተለይ ጎዳና የሚወጡ ዜጎች ሆነዋል።

ኃላፊዋ የችግሩን አሳሳቢነት በመገንዘብ በአዲስ አበባ ከተማ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ በኩል የሚወጡት ምን ዓይነት የሕብረተሰብ ክፍሎች እንደሆኑ፤ በምን ምክንያት እንደሚወጡ፤ ከየት አካባቢ እንደሚመጡ የሚያመላክት ሁኔታን ያካተተ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ በኩል ማስጠናቱን ይናጋራሉ።በጥናቱ እንደተመላከተው ታዲያ ጎዳና ላይ የማናየው የሕብረተሰብ ክፍል የለም።ሴቶች፤ ወጣቶች፤ አረጋውያን፤ ሕፃናት፤ የአካል ጉዳተኞች ሁሉም ዓይነት የሕብረተሰብ ክፍሎችን እናስተውላለን።ምክንያታቸው ምንድነው ከተባለ በአብዛኛው የኑሮ ውድነት ነው።ኑሮውን መቋቋም ባለመቻላቸው ነው የሚወጡት።በተለይ ታዳጊዎችና ወጣቶች ከቤተሰብ ጋር በመጋጨት በድርቅ፤ በጦርነትና ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ክስተቶች በፍልሰት ከሌሎች ክልሎችም እንደሚወጡ ታይቷል። ከአዲስ አበባ ከተማ የወጡም ይገኙበታል።የአዲስ አበባዎቹ ቁጥራቸው በአጠቃላይ በመዲናዋ ከሚገኙትና ጎዳና ከወጡት 50 ሺህ ዜጎች ውስጥ አምስት በመቶውን እንደሚይዝ ጥናቱ ማሳየቱን ኃላፊዋ ያነሳሉ።የነዚህ ዜጎች ወደ ጎዳና መውጣት በአዲስ አበባ ነዋሪዎች ላይ ያስከተለው መዘዝ ዘርፈ ብዙ እንደሆነም ይናገራሉ።ከፍተኛ የኑሮ ጫና ማስከተሉ ዋናው እንደሆነ የሚጠቅሱት ኃላፊዋ ወደ ጎዳና የወጡት አምስት በመቶ የአዲስ አበባ ከተማ



ወይዘሮ እታገኝ አሰፋ


ነዋሪዎች የመውጣታቸው መንስኤ ይሄው እንደሆነም መገመት እንደሚቻልም ይናገራሉ።መዘዙ በነዋሪው ላይ የምግብ፤ የመኖሪያ ቤት፤ የመጠጥ ውሀ አቅርቦትና ፍላጎቶች ላይ ከፍተኛ ጫና እያስከተለ ይገኛል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጫናውን በማቃለል ችግሩን ለመቅረፍ በተለይ ከክልል ፈልሰው ወደ አዲስ አበባ የመጡትን ወደ የመጡበት አካባቢ የመመለስ ሥራ በተደጋጋሚ ሲያከናውን መቆየቱንም ያስታውሳሉ።ተግባሩ ሲከናወን የነበረው የሚናገሩትን ቋንቋ መሰረት በማድረግ ነው ነገር ግን አማርኛ የሚናገር ሁሉ ከአማራ ክልል መጥቶ ላይሆን ይችላል፤ ከንባትኛ እየተናገረ ከሌላ ክልል ሊመጣም ይችላል።በመሆኑም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚናገሩትን ቋንቋ መሰረት አድርጎ የመጡበት ብሎ ወደሚገምተው ክልል በሚመልሳቸው ወቅት ክልሎቹ የኛ ስላልሆኑ አንቀበልም ስለሚሉ ሁኔታውን ፈታኝ አድርጎታል እንደ ኃላፊዋ ገለጻ።በሌላ በኩልም ስራው ከፍተኛ በጀት የሚጠይቅም መሆኑን ያብራራሉ።

ለጊዜው እነዚህን የሕብረተሰብ ክፍሎች ለመሰብሰብ ማገገሚያ ተቋማት እንዲገቡ እየተደረገ ነው።በዚህ ምክንያት ለጊዜው አብዛኞቹ ወደ ጎዳና የወጡ የሕብረተሰብ ክፍሎች ወደ ማገገሚያ እንዲገቡ ይሆናል።ሆኖም በቂ ማረፊያ ይህ ብቻውን በቂ ባለመሆኑ ችግሩን በጊዜ እንዳይቀረፍ አድርጎታል ይላሉ።

በአጠቃላይ ጎዳና የወጣውን የሕብረተሰብ ክፍል ለማንሳት በቅድሚያ ጎዳና በቂ በጀት አለ ወይ፤ የሰው ኃይል በቂ ነው ወይ፤ በቂ ማቆያ አለው ወይ? የሚለውን ማየት ያስፈልጋል የሚሉት ኃላፊዋ መሥሪያ ቤታቸው ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍ ባለፈው ያስጠናውን ጥናት መነሻ በማድረግ በቅርብ የመወያያ ጽሑፍ ማዘጋጀቱንም አንስተዋል።ጽሑፉ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ቀርቧል ብለዋል።በርካታ የሕብረተሰብ ክፍሎች በችግር ተጋልጠው ወደ ጎዳና መውጣት ጉዳይ የአንድ ከተማ አስተዳደር ችግር ስላልሆነ የክልል ፕሬዚዳንቶች በሙሉ ባሉበት ጽሑፉ ቀርቦም ውይይት ይደረግበታል። ሁሉም ኃላፊነቱን እንዲወስድ ለማድረግ ይረዳል ብለው ያምናሉ።ሁሉም ሰው ከተረባረበበት ችግሩ ሊቀንስ ይችላል ያሉት ኃላፊዋ ችግሩን ከምንጩ ለማድረቅ ቤተሰብ ላይ በትኩረት መሥራትና ለፍልሰቱም ለጎዳ ሕይወቱም ምክንያት የሆኑትን ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች በተቻለ መጠን ተረባርቦ መቀነስ መፍትሄ እንደሚሆንም መክረዋል።እኛም መፍትሄው እንዳሉት የሁሉንም ርብርብ የሚጠይቅ በመሆኑ እንረባረብ መልዕክታችን ነው።

# ዓለም አቀፍ



## በአሜሪካ አደገኛ ነው የተባለ ፈንገስ በከፍተኛ ሁኔታ እየተዛመተ ነው ተባለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በአሜሪካ ካንዲዳ ኦረስ የተባለ ፈንገስ በስፋት እየተዛመተ ነው ሲል የአገሪቱ የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከል (ሲዲሲ) አስታወቀ።

ይህ የፈንገስ ኢንፌክሽን ሰዎችን አንዴ ከያዘ ገዳይ ነው፤ ለማከም መድኃኒት በተሰጣቸው ታማሚዎች ላይ ለውጥ አልታየም።

ይህ ‘ፈንጋል ኢንፌክሽን’ ከአውሮፓውያኑ 2021 ጀምሮ በአሜሪካ ብቻ የተጠቂዎች ቁጥር ከ756 አሁን ወደሚገኝበት አንድ ሺህ 471 ደርሷል።

ጤነኛ ሰዎች በዚህ የፈንገስ በሽታ አይጠቁም። ይሁንና ሆስፒታል አካባቢ በተለይም በጽኑ የሕሙማን ክፍል የሚገኙ፤ በሰው ሰራሽ የመተንፈሻ መርጃ መሳሪያ (ቬንትሌተር) እገዛ የሚተነፍሱ፣ እንዲሁም የበሽታ መከላከል አቅማቸው የተዳከሙ ሰዎች ለዚህ የተጋለጡ ናቸው።

በተለይም በዕድሜ የገፉ ሰዎች ለካንዲዳ ፈንገስ ተጋላጭ ናቸው። በዚህ የፈንገስ በሽታ የሚያዙ ሰዎች ብዙዎቹ ለሚሰጣቸው የፀረ ፈንገስ መድኃኒት ምላሽ አይሰጡም። በዚህ የተነሳም አንዴ ከተያዙ ለመፈወስ አይችሉም።

ይህም በመሆኑ ነው የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከል (ሲዲሲ) በማገገሚያ ማዕከላት እና በሆስፒታሎች ውስጥ ልዩ ጥንቃቄ እንዲደረግ ያዘዘው። በዚህ የፈንገስ ተህዋሲ የተያዙ ሰዎች የሚሰጣቸው መድኃኒት ኢቺኖካንዲንስ (echinocandins) የተባሉ ሲሆን፣ ነገር ግን አብዛኞቹ ታማሚዎች መድኃኒቱ አልሠራላቸውም።

ለዚህ ፈንገስ መዛመት ዋና ምክንያት ተብሎ የተቀመጠው በሆስፒታሎች አካባቢ የሚታይ ደካማ የሆነ የኢንፌክሽን መከላከል ተግባር ነው። ሌላው ምክንያት ደግሞ በኮቪድ ተህዋሲ መዛመት የተነሳ በተፈጠረ መጨናነቅ የጤና ማዕከላት ተገቢውን የንጽሕና እና መሣሪያዎችን የማጽዳት ሂደትን መከተል በማቆማቸው ሊሆን እንደሚችል ተገምቷል።

ከአሜሪካ በተጨማሪ በሌሎች አገሮችም ካንዲዳ ኦረስ ፈንገስ ታይቷል። ባለፈው ዓመት የዓለም ጤና ድርጅት ይህን ፈንገስ “በመዛመት ቅድሚያ የያዘ አደገኛ ኢንፌክሽን” ሲል መድቦት ነበር ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

## የቻይና እና ሩሲያ ወዳጅነት ያስደነገጣቸው ምእራባውያን 16 ቢሊዮን ድጋፍ ለኪየቭ ሊሰጡ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



የወቅቱ የቻይናው መሪ የሞስኮ ጉብኝት በአሜሪካ እና አጋሮቿ ዘንዳ ከፍተኛ ድንጋጤ የፈጠረ ነው ተብሏል፡፡

“ገደብ የለሽ” ግንኙነት እንዲኖራቸው ከስምምነት የደረሱት የቻይና እና ሩሲያ መሪዎች ወዳጅነት ለምእራባውያን እጅግ አሳሳቢ ሆኖ የመጣ ጉዳይ ሆኗል፡፡

በተለይም ከዩክሬን ጦርነት ጋር በተያያዘ ዓለም በሩሲያ ላይ ሲረባረብ ቻይና የምታራምደው የተለየ አቋም የቤጂንግ-ሞስኮ ግንኙነት እጅግ የጠበቀ መሆኑ የሚያመላክት እንደሆነ ይነሳል፡፡

ሩሲያ፤ ቻይና በደም አፋሳሹ የዩክሬን ጦርነት ጉዳይ የምታራምደው አቋም ሚዛናዊ ነው ብላ ብታምንም አሜሪካና ምእራባውያን አጋሮቿ ነገሩን በጥርጣሬ እንደሚያዩት ሲገልጹ ይደመጣሉ፡፡

የወቅቱ የቻይናው መሪ የሞስኮ ጉብኝት ያስደነገጣት አሜሪካ ፕሬዚዳንት ሺ ጂንፒንግ እውነት ካላቸው በፑቲን ላይ ጫና በመፍጠር ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ በአውሮፓ ትልቁን ግጭት እንዲቆም ያድርጉ ስትልም ተደምጣለች፡፡

ፕሬዚዳንት ሺ የሩሲያው አቻቻው ፑቲን የዩክሬንን ሉዓላዊነት እንዲያከብሩ ሊነግሯቸው ይገባልም ነበር ያለችው ዋሽንግተን፡፡

ነገር ግን የፕሬዚዳንቱ የሁለት ቀን የሞስኮ ቆይታ አሜሪካ እና አጋሮቿ እንዳሰቡት ሳይሆን መሪዎቹ የሁለትየሽ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር የመከሩበት ጥሩ አጋጣሚ ሆኖ ማለፉ እየተነገረ ነው፡፡

መሪዎቹ ዋሽንግተን ለዓለም ሰላም ጠንቅ እየሆነች መምጣቷን እንዲሁም አሁን ላይ ኔቶን ሽፋን በማድረግ ወደ እስያ-ፓሲፊክ ቀጠና ለመግባት እየሞከረች መሆኗ በተመለከተም መምከራቸውም ባወጡት የጋራ መግለጫ አስታውቀዋል፡፡

በተለይም የቻይናው ፕሬዚዳንት የሞስኮ አቻቸው ቭላድሚር ፑቲንን አሞካሹ የሚለውን ዜና መሰማቱ ምእራባውያንን ያስደነገጠ ሆኗል፡፡

ጉብኝቱ መፍትሄ የሚያመጣ ሳይሆን ለአንድ ዓመት የዘለቀውን ደም አፋሳሹን የዩክሬን ጦርነት የሚያበረታታ ነው ሲሉም ተችተውታል፡፡ በዚህም የቻይና እና ሩሲያ ወዳጅነት ያስበረገጋቸው ምእራባውያን ለኪየቭ ተጨማሪ ገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ወስነዋል፡፡

ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም (አይ.ኤም.ኤፍ) በጦርነት ለተጎዳችው ኪየቭ ለአራት ዓመታት የሚቆይ የ15 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ዶላር የብድር ፓኬጅ ለማመቻቸት ቅድመ ስምምነት መደረጉን አስታውቋል።

ገንዘቡ ለአንድ ዓመት በዘለቀው ጦርነት በሩሲያ ኃይሎች መሰረተ ልማቶቿ እና በኢኮኖሚዋ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባትን ዩክሬን ለማገዝ ያለመ ነው ተብሏል፡፡

ምእራባውያን ዩክሬንን መደገፋቸው አጠናክረው ቢቀጥሉበትም የሩሲያው ፕሬዚዳንት ምዕራባውያን ለኪየቭ የሚያደርጉት ገንዘብም ሆነ ጦር መሳሪያ ድጋፍ ጦርነቱን ከማባበስና የዜጎችን ሰቆቃ ከማራዘም በዘለለ ምንም ፋይዳ እንደሌለው ተናግረዋል፡፡

ፑቲን ከሺ ጋር ባደረጉት ስብሰባ በኋላ በሰጡት አስተያየት፤ ብሪታኒያ ዩራኒየም የያዙ ታንክ ጥይቶችን ወደ ዩክሬን ለመላክ ማቀዷን አውግዘዋል፤ ውጤቱንም የከፋ እንደሚሆንም አስጠንቅቀዋል።

“ይህ ሁሉ የሚሆን ከሆነ ሩሲያውያን ምላሽ መስጠት አለባቸው፤ ምክንያቱም ምዕራባውያን በጋራ ሆነው የኒውክሌር ቁሳቁስ ያላቸውን የጦር መሳሪያዎች መጠቀም ጀምረዋል” ብለዋል የሞስኮው ኃያል ሰው ፑቲን ሲል የዘገበው አል አይን ኒውስ ነው፡፡

# ስፖርት



## ኢትዮ-ኤሌክትሪክ በአጭር ርቀትና የሜዳ ተግባራት ውድድሮች ላይ አተኩሯል

አስማየሁ ግዛው

በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተለያዩ ውድድሮች ጠንካራ ተፎካካሪና ውጤታማ ከሆኑ ክለቦች መካከል ኢትዮ-ኤሌክትሪክ በቀዳሚነት ይጠቀሳል። በዚህም ውጤታማነቱ በዓለም አቀፍ መድረኮች ኢትዮጵያን ወክለው ውጤታማ የሆኑ በርካታ ከዋክብት አትሌቶችን እያፈራ ይገኛል።

የኢትዮ- ኤሌክትሪክ ይህን ውጤታማነቱን አጠናክሮ ለመቀጠል በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አማካኝነት ለሚዘጋጁ ቀጣይ ውድድሮች ጠንካራ ዝግጅቶችን በማድረግ ላይ እንደሚገኝ አስታውቋል። ክለቡ እየተካሄደ በሚገኘው የኢትዮጵያ የአጭር፣ የመካከለኛና የሜዳ ተግባራት ውድድር እንዲሁም ለ52ኛው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ጠንካራ ዝግጅት ማድረጉን ገልፆ፣ በነዚህ አገር አቀፍ ውድድሮች ውጤታማ ከመሆን ባሻገር አገርን የሚወክሉ ጠንካራ አትሌቶችን ለማፍራት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል።

ክለቡ ከዚህ በፊት በአሰላ፣ ድሬዳዋና ደብረ ብርሃን በተካሄዱ አገር አቀፍ ውድድሮች ጥሩ ውጤቶችን ማስመዝገብ እንደቻለ የሚታወስ ሲሆን፣ በቀጣይም የተሻለ ውጤት ለማምጣት ጠንካራ ስራዎችን በመስራት ላይ መሆኑን ጠቁሟል። ለዚህም ክለቡ አትሌቶቹን በሜዳ፣ በመምና በጅምናዚየም ታግዞ እያዘጋጀ ይገኛል።

ኢትዮ ኤሌክትሪክ ኢትዮጵያ ውጤታማ ባልሆነችባቸው በአጭር፣ መካከለኛና የሜዳ ተግባራት ውድድሮች በአገር አቀፍ ደረጃ ውጤት ከማስመዝገብ አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃ ውጤታማ የሚሆኑ አትሌቶችን ለማፍራት በትኩረት እየሰራ እንደሚገኝ አስታውቋል። በነዚህ የውድድር አይነቶች የምስራቅ አፍሪካ አገራት ብዙም ያልተሰራባቸው ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኬንያ ትኩረት ሰጥታ በመስራቷ ተስፋ ሰጪ ውጤት እያስመዘገበች ትገኛለች። አትዮጵያም ትኩረት ሰጥታ ከሰራች ከምትታወቅበት የረጅም ርቀት ውድድሮች በተጨማሪ ውጤት ማምጣት ትችላለች በሚል እምነት ኢትዮ ኤሌክትሪክ እየተንቀሳቀሰ ነው።

በአገር ውስጥ በሚደረጉ ውድድሮች ኢትዮ ኤሌክትሪክ በሚያስመዘግባቸው ዉድድሮች የተሻሉ ውጤቶችን ማስመዝገብ እንደሚቻል ማሳየት ችሏል። ክለቡ ከተለመዱት የውድድር አይነቶች ውጪ በአጭር ርቀትና በሜዳ ተግባራት ውድድሮች በኦሊምፒክ ደረጃ ውጤት ማምጣት የሚችል አትሌት ማፍራትን አላማው አድርጎ እየሰራ እንደሚገኝ ገልጿል። በዚህም በአገር አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ ውድድሮች የክለቡ አትሌቶች አመርቂ ውጤቶችን በማስመዝገብ ተስፋ እያሳዩ እንደሚገኙ ተጠቁሟል።

ክለቡ ከአትሌቲክስ በተጨማሪ በሁሉም የስፖርት አይነቶች የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ የቻለው ባደረገው መሰረታዊ የአስተዳደር ለውጦችና ወደ ክለቡ በቀላቀላቸው ባለሙያዎች መሆኑን ጠቁሟል። ባለሙያዎቹ ልምዳቸውና እውቀታቸውን በማጣመር ሳይንሳዊ የሆነ ስልጠናን በመስጠት አትሌቶቹ ለድል እንዲበቁ አሰተዋጾኦን እንዳበረከቱም ያምናል።

ክለቡ ይህን አጠናክሮ ለመቀጠል ታዳጊዎችን በመመልመልና በስልጠና ሂደቱ እንዲያልፉ በማድረግ ላይም ይገኛል።

ኢትዮ ኤሌክትሪክ በርካታ ታላላቅና የኢትዮጵያን ባንዲራ በዓለም አደባባይ ያውለበለቡ ኮከብ አትሌቶችን ማፍራት ችሏል። ከቀድሞዎቹ የክለቡ ስኬታማ አትሌቶች መካከል አትሌት ጂኣ ይሳቅ፣ መሰለች መልካሙ የሚጠቀሱ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅትም በሪሁን አረጋዊ፣ ታደሰ ወርቁና ሌሎች ስኬታማ አትሌቶች ባለቤት ነው። የቀድሞ የክለቡ ስኬታማ አትሌቶችም አሁን ላይ ልምድና እውቀታቸውን ተጠቅመው ክለቡን በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ለክለቡ ውጤት ማማርም የአንጋፋ አትሌቶቹ ድርሻ ቀላል እንዳልሆነ ተገልጿል።

ክለቡ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ባደረጋቸው ለውጦች የውጤት መነቃቃት እንዲፈጠር ያደረገ ሲሆን፣ ለአትሌቶቹ ውድድር በማዘጋጀት ወቅታዊ ብቃታቸውን የመፈተሽና የተሻለ ብቃት ያላቸውን አስቀርቶ ጥሩ ያልሆኑትን የመቀነስ ስራ በዋናነት ተሰርቷል።

ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችን በማወዳደር የሟሟላት ስራም በስፋት የተሰራ ሲሆን፣ በዚህም በየውድድር አይነቱና ተግባሩ ዋና ባለሙያ፣ ዋና አሰልጣኝ፣ ምክትል አሰልጣኞች ተቀጥረው ውጤታማ ስራዎችን በማከናወን ላይ እንደሚገኙ ተጠቁሟል። በተጨማሪም ለአትሌቶችና ባለሙያዎች የደሞዝ ማሻሻያ የተደረገ ሲሆን፣ የአደረጃጀት ለውጦች ክለቡን ውጤታማ ሆኖ እንዲጓዝ አስችለውታል።

የአትሌቶች የስልጠና ሂደት ሳይንሳዊ ከመሆኑ ባሻገር ለስልጠና የሚሰጠው ትኩረት ከፍተኛ መሆኑም ክለቡ በርካታ አገርን መወከል የሚችሉ አትሌቶችን ለማፍራት እንዳገዘው ተጠቁሟል።

ክለቡ የራሱ የሆነ ማዘወተርያ ስፍራ ቢኖረውም በየውድድር አይነቱ እንደአስፈላጊነቱ የተሟላ ባለመሆኑ ፈታኝ ነገሮችን መጋፈጡ አልቀረም። ለዚህም መፍትሔ እንዲሆን ክለቡ በቀጣይ የራሱን የስፖርት አካዳሚ ለመገንባት እቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ ጠቁሟል። ለዚህም የግንባታ ፕሮፖዛል እየተዘጋጀ ሲሆን የግንባታው ቦታው የት እንደሚሆን ግን ውሳኔ ላይ አልተደረሰም። ለትግበራው ጥናት ከተደረገ በኋላ ወደ ስራ ለመግባት መታቀዱን ግን ከክለቡ ለማወቅ ተችሏል።


## የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

1. የንግድ ምልክት ባለቤት፡ Hermes International አድራሻ፡ 24, rue du Fauborg Saint-Honore, 75008 Paris, France
2. የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/ 7024
3. የጥበቃ ጊዜው፡ 13/1/2023 እስከ 13/1/2030
4. የንግድ ምልክት፡



5.ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በቀን 19/06/2008 Vol.LXXV No.169 እና በኢትዮጵያ ሄራልድ በቀን 24/02/2016 Vol.LXXII No.142 በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው።
6.ይህ የንግድ ምልክት የታደሰ በመሆኑም ማንኛውም ሰው ከባለቤቱ ፍቃድ ውጭ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**
**ADDIS ZEMEN VOL - LXXXII No-194 14/7/2015 (23/3/2023)**

## የስምና አድራሻ ለውጥ ማስታወቂያ

Shenzhen Oneplus Technology Corp., Ltd. በ Room A201, Complex Building of Qianhai SZ-HK Cooperation Zone Administration Bureau, 1 Liyumen Street, 1 Qianwan Road, Qianhai SZ-HK Cooperation Zone, Shenzhen, Guangdong, China የሆነ፣ ሕጋዊ ስሙንና አድራሻውን ወደ One PlusTechnology (Shenzhen) Co., Ltd., 18C05, Shum Yip Terra Building, Binhe Avenue North, Futian District, Shenzhen, Guangdong, China መለወጡን ያስታውቃል።

ስለሆነም ኩባንያው በማመልከቻ ቁጥሮች FTM/7395 እና FTM/7396 ለተመዘገቡት የንግድ ምልክቶች በአዲሱ በአዲሱ ስም ባለቤትነቱንና ተጠቃሚነቱን በኢትዮጵያ ቀጥሏል

oneplus

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**
**ADDIS ZEMEN VOL - LXXXII No-194 14/7/2015 (23/3/2023)**

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

1. የአመልካች ስምና አድራሻ Enetek Power Group Fte Ltd8 Pandan Crescent #04-03, 128464, Singapore
2.የማመልከቻ ቁጥር፥ FTM/013964 ቀን 23/12/2022
3. የንግድ ምልክቱ ስዕላዊ መግለጫ የቃል እና የስዕል
4. ምልክት

enetek +POWER-

5. የቀለም ዓይነት "ቀይ፣ ግሬይ"
6.የብቸኛነት መብት ያለመጠየቅ መግለጫ "POWER"
7.ዓለም አቀፍ ምድብ 09
8. ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች

-ባትሪዎች፤ የባትሪ መሙያዎች፤ ሪክቲፋየርስ፤ የኃይል አቅርቦት አሃዶች (ሪክቲፋየርስ)፤ የማይቋረጥ የኃይል አቅርቦት መሳሪያ የማይቋረጥ የኃይል አቅርቦት መሳሪያዎች የማይቋረጥ የኃይል አቅርቦት መሳሪያ (ባትሪ)፤ለኃይል አቅርቦት ኢንቨርተሮች፣ ታይርስቶር የመቀየሪያ ሁኔታ የኃይል አቅርቦት መሳሪያ (ኤሌክትሪክ)፤ ትራንስፎርመር ክፍሎች፤ የባትሪ ክፍያ መቆጣጠሪያዎች፡፡

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል: ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታወቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ከባለቤቱ ፈቃድ ውጪ በዚህ ምልክት የሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በሕግ ክስ ይመሰረትበታል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**
**ADDIS ZEMEN VOL - LXXXII No-194 14/7/2015 (23/3/2023)**

## የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

| | |
|---|---|
| 1. | የንግድ ምልክት ባለቤት ስምና አድራሻ Rolex S.A. rue Francois-Dussaud 3-5-7, 1211 Geneva 26, Switzerland |
| 2. | የማመልከቻ ቁጥር FTM/6949 |
| 3. | የጥበቃ ጊዜው፡ ከ16/12/2022 እስከ 16/12/2029 |
| 4. | ምልክት |
| 5. | ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በአዲስ ዘመን VOL. LXXV No.169 በ19/06/2008 ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎች ነው፡፡ |
| 6. | ይህ የንግድ ምልክት የታደሰ በመሆኑም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡ |

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**
**ADDIS ZEMEN VOL - LXXXII No-194 14/7/2015 (23/3/2023)**